# የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

# 140ኛ ልዩ መግለጫ



**በመንግሥት የጸጥታና ታጣቂ ኃይሎች በዜጎች ላይ የሚፈጸም አሠቃቂ ግድያ፣ ሕገ-ወጥ እሥር፣ ድብደባ፣ ማስፈራራትና ማዋከብ በአስቸኳይ ይቁም!!**

መጋቢት 5 ቀን 2008 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

የምዝገባ ቁጥር 1146
www.hrco.org.et

# ሰመጉ

## ዋናው ጽ/ቤት፡ አዲስ አበባ


አ.አ ስታዲየም አጠገብ ላሊበላ ሬስቶራንት ጎን፣ ሣኅለ ሥላሴ ሕንፃ 8ኛ ፎቅ፣ ቢሮ ቁጥር 19

ስልክ: (+251) 011 551-7704

ፋክስ: (+251) 011 551-7704

ኢሜይል: info@hrco.org.et

ድረ ገጽ: www.hrco.org.et

የፖስታ ሳጥን ቁጥር 2432

አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ

## የሰብዓዊ መብቶች ክትትል እና ምርመራ መምሪያ

ስልክ: (+251) 011 558-2387

ኢሜይል: monitoringcomplaints@hrco.org.et

## ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች

ሐዋሳ (ደቡብ ኢትዮጵያ ቀጠና)፡ ስ.ቁ (+251) 046 220-4500፣ ፖ.ሳ.ቁ 360

ባሕርዳር (ሰሜን ኢትዮጵያ ቀጠና)፡ ስ.ቁ (+251) 058 226-3913፣ ፖ.ሳ.ቁ 1115

ነቀምቴ (ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና)፡ ስ.ቁ (+251) 057 661-5014፣ ፖ.ሳ.ቁ 463

ድሬደዋ (ምሥራቅ ኢትዮጵያ ቀጠና)፡ ስ.ቁ (+251) 025 811 9150 ፖ.ሳ.ቁ 2596


ጅማ (ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና)፡ ስ.ቁ (+251) 147 211 5434

አዲስ አበባ (ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቀጠና)፡ ስ.ቁ (+251)011 551-7704፣ ፖስታ ሳጥን ቁጥር 2432

# ማውጫ

1. የኢትዮጵያ አስተዳደር ክልል እና ዞን ካርታ --------------- --------------------------- 1
2. የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ --------------------------------- ----------------------------------- 2
3. መግቢያ ---------------------------------------------------------------------------- 3
3.1 የምርመራ ሥራው የሸፈናቸው ዞኖችና ወረዳዎች ------------------------------- 4
3.2 የመረጃ ምንጮችና የምርመራ ዘዴዎች ---------------------------------------- 5
3.3 በምርመራ ሥራው ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ------------------------------ --------- 5
4. የመጀመርያው የተቃውሞ መነሻ ---------------------------------------- 5
5. በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ አካባቢዎች የደረሰው ጉዳት -------------------------- 6
5.1 ግድያ ------------------------------------------------------------------------------ 6
5.2 በጥይት ማቁሰል፣ ድብደባና ማሠቃየት -------------------------------------- 16
5.3 ማሠቃየትና ድብደባ ---------------------------------- ------------------------------- 25
5.4 እሥራት --------------------------------- ------------------------------------------ 36
5.5 የደረሱበት የማይታወቅ ---------------------------------- -------------------------- 28
5.6 የንብረት ውድመትና መፈናቀል ------------------------------------------------------------ 28
5.7 የወደመ የመንግሥት ንብረት ------------------------------------------------------- 30
6. ማጠቃለያ --------------------------------------------------------------------------------------- 31
7. ማሳሰቢያ ------------ ------------------------------------------------------------------ 32
አድራሻዎች --------------------------------- ------------------------------------------ 32

# 1. የኢትዮጵያ አስተዳደር ክልል እና ዞን ካርታ[1]




የመብት ጥሰቱ የተፈጸመባቸው አካባቢዎች

[1] “ኢትዮጵያ” [ካርታ]. <http://www.h2empower.org/aboutus/factsethiopia.html>. (August 11, 2015)

## 2. የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ሰመጉ)፣ የቀድሞው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) በኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር አንቀጽ 1(ሀ) እና በኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር ከ404-482 በተጻፉት ድንጋጌዎች መሠረት መስከረም 29 ቀን 1984 ዓ.ም. በአባላት የተመሠረተ የመጀመሪያው መንግሥታዊ ያልሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ተቋም ነው፡፡ ሰመጉ በበጎ አድራጎትና ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001 መሠረት "ኢትዮጵያዊ የበጎ አድራጎት ማኅበር" ሆኖ በምዝገባ ቁጥር 1146 በሕጋዊነት በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ ድርጅት ነው፡፡ ሰመጉ ከማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲ፣ የኃይማኖት ተቋም፣ የብሔረሰብ ቡድን፣ ማህበራዊ መደብ ወዘተ የማይወግን፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ነጻና ገለልተኛ የሆነ የሰብአዊ መብቶች ተከላካይ ተቋም ነው፡፡ ሰመጉ የቆመው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መጎልበት፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነው፡፡

ሰመጉ ላለፉት 24 ዓመታት በቆመላቸው ዐበይት ዓላማዎች ላይ በመመርኮዝ፣ ሁለንተናዊ ሐገራዊና ሕዝባዊ ተልዕኮ በመያዝ በነደፋቸው በርካታ የመርሐ-ግብር ተግባራት አማካኝነት ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ የሕግ የበላይነት እና ሕጋዊ ሥርዓት እንዲሰፍንና በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲኖር የበኩሉን አስተዋጽዖ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡

ዓበይት ዓላማዎቹንና ተልዕኮውን ለማሳካት ሰመጉ ፈርጀ ብዙ የሆኑ የመርሐ ግብር ተግባራትን ያከናውናል፡፡ ከነዚህም መካከል አንዱ በየደረጃው ለሚገኙ የመንግሥት አስፈጻሚ አካላትና ለሕዝብ የሰብዓዊ መብቶች ትምህርትና ሥልጠና መስጠት ነው፡፡ የመንግሥት አካላት በዋነኛነት የግዴታዎች ተሸካሚ፣ ሕዝብም በዋነኛነት የመብቶች ባለቤት እንደመሆናቸው መጠን፣ የመንግሥት አካላትም መብት የማክበርና የማስከበር ግዴታቸውን በዕውቀት፣ በችሎታና በጽኑ እምነት ላይ ተመርኩዘው እንዲወጡ፣ ሕዝብም እንዲሁ በዕውቀት፣ በችሎታና በጽኑ እምነት ላይ ተመርኩዞ መብቱን እንዲያስከብር ሰመጉ የሰብዓዊ መብቶች ትምህርትና ሥልጠና ይሰጣል፡፡

የሰመጉ መለያውና ግንባር ቀደም ተግባሩ በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶችን አያያዝና ሁኔታ መከታተል፣ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ማጣራትና በማስረጃ የተደገፉ መግለጫዎችን ማውጣት ነው፡፡ ሰመጉ በሚያወጣቸው መግለጫዎች ሁሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች ፍትሕና ካሣ እንዲያገኙ፣ የጥሰት ፈጻሚዎች በሕግ እንዲጠየቁና ወንጀል ሠርቶ በነጻ መሄድ እንዲያበቃ፣ ከእያንዳንዱ ክስተት ትምህርት ተወስዶ ለወደፊቱ ጥንቃቄና እርማት እንዲደረግ ሲጮህና ሲጠይቅ ቆይቷል፣ አሁንም በመጠየቅ ላይ ነው፤ ለወደፊትም በዚሁ ይቀጥላል፡፡

በተጨማሪም በተለይ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ሰለባ ለሆኑ ዜጎች የተለያየ ደረጃና መልክ ያለው የሕግ ድጋፍ መስጠት፣ በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ማከናወንና ውጤቶቹን በስብሰባዎችና በልዩ ልዩ የመገናኛ መንገዶች ማሠራጨትና የአድቮኬሲ ሥራዎችን መሥራት፣

በመንግሥት የወጡና የሚወጡ ሕጎች ይዘትና አፈጻጸማቸውን መከታተል፣ የሕግ ታራሚዎችን መጎብኘትና ሰብዓዊ መብቶቻቸው መጠበቃቸውን መከታተልና የፍርድ ቤቶችን ሂደት መከታተል  የሰመጉ ዋና ዋና ተግባራት ናቸው።

በእስካሁኑ ቆይታው ሰመጉ 36 መደበኛ መግለጫዎችና 139 ልዩ መግለጫዎችን በተጨማሪም በተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በርካታ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ይፋ አድርጓል። ሰመጉ አሁን በሚገኝበት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖም ቢሆን፣ ሁኔታና ዐቅም በፈቀደለት መጠን የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ የሕግ የበላይነትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በኢትዮጵያ እውን እንዲሆን ካለው የጸና ዓላማ አኳያ በመሥራት ላይ ይገኛል።

## 3. መግቢያ

የአዲስ አበባና የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን የተቀናጀ ማስተር ፕላን በፊንፊኔ ዙሪያ ባሉ የኦሮሚያ ከተሞችና የገበሬ ማኅበር መንደሮች ማፈናቀል ስለሚፈጥር ማስተር ፕላኑን እንቃወማለን በማለት በኦሮሚያ ክልል ባሉ የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች የሚማሩ ተማሪዎች ከሚያዚያ ወር 2006 ዓ.ም ጀምሮ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ አካሂደዋል። ዳሩ ግን የተማሪዎቹ ጥያቄ ምንም ይሁን ምን በሰላማዊ ሰልፉ ላይ ለተነሡት ጥያቄዎች መንግሥት በሰላማዊ መንገድ መልስ መስጠት ሲገባው ይህንን ሕገ መንግሥታዊና ዓለም አቀፋዊ አስገዳጅ ድንጋጌ በመተላለፍ በመንግሥት ኃይሎች በተፈጸሙ ሕገ ወጥ ግድያና እሥር ዜጎች ለሕልፈተ ሕይወትና ለእንግልት መዳረጋቸውን፣ በንብረት ላይም ከፍተኛ ጉዳት መድረሱን አስመልክቶ የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ 132ኛ ልዩ መግለጫ ማውጣቱ ይታወሳል።

ኢትዮጵያ የተቀበለችው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 3 እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖር መብት እንዳለው ያረጋግጣል። ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችውና ፍጹም አስገዳጅ የሆነው የሲቪልና የፖሊቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳንም በአንቀጽ 6 ንዑሥ አንቀጽ 9 ላይ እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖር ተፈጥሮአዊ መብት እንዳለው ይደነግጋል። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥትም ይህንኑ በሕይወት የመኖር መሠረታዊ መብት በአንቀጽ 15 ላይ ያረጋግጣል። በተጨማሪም ይህ መብት የማይደፈርና የማይገሠሥ መሆኑን የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 14 ይደነግጋል። ይሁን እንጂ ይህንን ሕገ መንግሥታዊና ዓለም አቀፋዊ ድንጋጌ በመተላለፍ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በተለያዩ ዞኖችና ወረዳዎች ግድያ ተፈጽሟል።

ከኅዳር ወር 2008 ዓ.ም ጀምሮ የአዲስ አበባና የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን የተቀናጀ ማስተር ፕላንን በመቃወም በምዕራብ ሸዋ፣ በደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣ በፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን፣ በምዕራብና ምሥራቅ ወለጋ፣ በሆሮጉድሩ፣ በምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ፣ በባሌ፣ በአርሲ ዞኖችና በተለያዩ የኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች በሚገኙ በርካታ ከተሞች ተማሪዎችና ሕዝቡ የተቃውሞ ሰልፎች እያካሄዱ ይገኛሉ። የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች ለተቃውሞ በወጡ ዜጎች ላይ በወሰዷቸው ከመጠን ያለፉ የኃይል እርምጃዎች የበርካታ ዜጎች ሕይወት ጠፍቷል፣ በርካታ ሰዎች በጥይት ተመትተው የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፣ በርካታ ሰዎች ታሥረዋል፣ ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ ሰዎች የደረሱበት አይታወቅም፣ ከፍተኛ ኪሳራ ያስከተለ ከባድ የንብረት ውድመት ደርሷል።

ከዚህ በተጨማሪም ዜጎች ለሚያነሷቸው ማንኛውም ዓይነት ጥያቄዎች መንግሥት በሰላማዊ መንገድ መልስ ሊሰጥ እንደሚገባ ዕሙን ነው። ከዚህም አንጻር የኢፌዴሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 30(1) ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት እንዳለው ይደነግጋል።

የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ - ሰመጉ ‹‹ከአዲስ አበባና የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን የተቀናጀ ማስተር ፕላን ተቃውሞ ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በአስቸኳይ ይቁሙ!›› በሚል ርእስ ታኅሣሥ 11 ቀን 2008 ዓ.ም ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ ከተቃውሞ እንቅስቃሴው ጋር በተያያዘ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን መንግሥት በገለልተኛ አካል እንዲያጣራ፣ ለጥሰቱ ተጠያቂ የሆኑ አካላትን ለፍርድ እንዲያቀርብ፣ በግጭቱ ሳቢያ ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች ተገቢው ካሣ እንዲከፈል እንዲሁም ቤቶቻቸው ለተቃጠሉባቸው፣ ንብረት ለወደመባቸውና ከኑሯቸው ለተፈናቀሉ ዜጎችም መልሶ የማቋቋም ሥራ እንዲከናወን ጥሪውን ማቅረቡ ይታወሳል፡፡

ዜጎች ሕይወታቸውና ኑሯቸውን በሚመለከቱ የመንግሥት ዕቅዶች፣ ሕጎችና ፖሊሲዎች ላይ የመሳተፍ፣ የመወያየት፣ ሐሳብ የመስጠት፣ የመጠየቅና የመቃወም መብት እንዳለቸው በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ላይ ተደንግጓል፡፡ አሳታፊነት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት የመልካም አስተዳደር እና የሰብዓዊ መብቶች መከበር መሠረቶች መሆናቸውም ይታወቃል፡፡ መንግሥት የተቀናጀ የማስተር ፕላኑን በማርቀቅ ሂደት ዜጎችን በተለይም በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኙ የኦሮሚያ ገጠርና ከተማ ነዋሪዎችን ባለማሳተፉ፤ ረቂቅ ሠነዱንም እስከዛሬ ድረስ ለሕዝብ ይፋ ባለማድረጉ የብዙ ዜጎችን ሕይወት ለቀጠፈውና የአካልና የንብረት ጉዳት ላስከተለው ቀውስ ምክንያት ሆኗል፡፡ ረቂቅ ማስተር ፕላኑ ለባለሙያዎችና ለሌሎችም ባለድርሻ አካላት ቀርቦ ግልጽ ውይይት፣ ክርክር እና ትችት ሊደረግበት ሲገባ ለዓመታት በምሥጢር መያዙና ይዘቱም ለዜጎች አለመገለጹ ለጥርጣሬ፣ ለውዥንብርና ደም ላፋሰሰ ግጭት መንሥዔ ሆኗል፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ በጋዜጣዊ መግለጫው እንዳስታወቀው በግጭቱ የጸጥታ ኃይሎች ከመጠን ያለፈ ኃይል በመጠቀማቸው በዜጎች ላይ ሞትና የአካል መጉደል ስለመድረሱ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ ከተቃውሞው ጋር በተያያዘ የተከሰቱ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን በመመርመር ላይ እንደሚገኝ፤ ምርመራውም እንደተጠናቀቀ ሕዝብና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት መግለጫውን ይፋ እንደሚያደርግ መግለጹ ይታወሳል፡፡ በዚሁ መሠረት የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ ባለሙያዎቹን ችግር በተከሰተባቸው የተለያዩ ሥፍራዎች በመላክ በበቂ ማስረጃ ተደግፎ የተጠናቀረውን መግለጫውን እንደሚከተለው ይፋ አድርጓል፡፡

የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳደር በ18 ዞኖችና በ342 ወረዳዎች የተከፋፈለ ነው፡፡ በአብዛኛው በኦሮሚያ ዞኖችና ወረዳዎች የተቃውሞ እንቅስቃሴ ተደርጓል፡፡ የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ ባለው ውሱን አቅም የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት በደረሰባቸው የኦሮሚያ አካባቢዎች በሙሉ ተንቀሳቅሶ ለማጣራት አልቻለም፡፡ ሰመጉ ከፍተኛ ጉዳት ደረሰባቸው በተባሉ 33 ወረዳዎች ባለሙያዎቹን በመላክ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ምርመራ አከናውኗል፡፡ ይህ ልዩ መግለጫ የሚያካትተው ቀውሱ ከተከሰተበት ከህዳር እስከ የካቲት 12 /2008 ዓ.ም. ድረስ ሰመጉ ያደረገውን የመስክ ምርመራ ውጤት ብቻ ነው፡፡

### 3.1 በምርመራው ሥራ የተሸፈኑ የኦሮሚያ ዞኖችና ወረዳዎች

| | ምዕራብ ሸዋ ዞን | | ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን | | ምዕራብ ወለጋ ዞን | | ፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጨሊያ ወረዳ | 13 | አመያ ወረዳ | 22 | እናንጎ | 31 | ቡራዩ ከተማ |
| 2 | ባቢች | 14 | ወሊሶ | 23 | ጉሉሶ ወረዳ | 32 | ሱሉልታ ከተማ |
| 3 | ቶኬ ኩታይ | 15 | ጌዶ | 24 | ጫንቃ | | |
| 4 | አምቦ | 16 | ወንጪ | 25 | ደምቢዶሎ | | |
| 5 | ደንዲ | | ወለጋ ሆሮ ጉድሩ ዞን | | ምዕራብ ሀረርጌ ዞን | | ምዕራብ አርሲ ዞን |
| 6 | ሙገር | 17 | ጉድሩ ወረዳ | 26 | ሆርና | 33 | አዳባ |
| 7 | አድዓ በርጋ | 18 | ፍንጭ ውሀ | 27 | ሀሰቦት | | |
| 8 | ሜታሮቢ | 19 | ገበቴ | 28 | መሰላ | | |
| 9 | ግንደበረት | 20 | ፍንጭ ውሀ በረሀ | | | | |
| 10 | ኤልፋታ | | ምስራቅ ወለጋ ዞን | | ምስራቅ ሀረርጌ ዞን | | |
| 11 | ጀልዱ | 21 | ሳሲጋ | 29 | ባቲ | | |
| 12 | ወለንኮሚ | | | 30 | አወዳይ | | |

## 3.2 የመረጃ ምንጮችና የምርመራ ዘዴዎች

ሰመጉ በምርመራው ከተጠቀመባቸው የመረጃ ምንጮች መካከል ዋነኞቹ፣ የሰብዓዊ መብት ጥሰቱ ተጎጂዎች፣ የተጎጂ ቤተሰቦች፣ የዓይን እማኞችና ምስክሮች፣ ቀውሶቹ በተከሰቱባቸው አካባቢዎች ነዋሪ የሆኑ ዜጎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም ከመንግሥት ጉዳዮች ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት፣ ከፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ ከኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን፣ ከተወሰኑ የከተማ አስተዳደሮች፣ ከኦሮሚያ ክልል መስተዳድር፣ ከተወሰኑ የዞንና የወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤቶችም መረጃ ለማግኘት ሙከራ ተደርጓል፡፡

የሰመጉ ባለሙያዎች ወደ መስክ ምርመራ ከመሰማራታቸው በፊትና በኋላም ብዛት ያላቸውን ተዛማጅ ሠነዶች ፈትሸዋል፡፡ ከነዚህም መካከል የማስተር ፕላኑ ረቂቅ፣ ልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ተቋማትና የመገናኛ ብዙሐን ያቀረቧቸው ዘገባዎችና ግለልተኛ ምሁራን፣ መንግሥትና ተቃዋሚዎች የሰጧቸው መግለጫዎችና ትንታኔዎች ይገኙባቸዋል፡፡ ዋነኞቹ የምርመራ ዘዴዎች የሠነዶች ማሰባሰብና ፍተሻ፣ በፎቶግራፍ፣ በድምጽና በተንቀሳቃሽ ምስሎች የተደገፉ የመስክ ጉብኝቶች (ጥሰት በተፈጸመባቸው ቦታዎች በአካል በመገኘት)፣ ከተጎጂዎችና ከምስክሮች ጋር በቦታዎቹ ላይ የተደረጉ ቃለመጠይቆች፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ዜጎችና አካላት ጋር የተደረጉ የቡድን ውይይቶች ናቸው፡፡ ሰመጉ በዚህ ምርመራው የተለያዩ ማስረጃዎችን በማሰባሰብና ጉዳቱንም በመመልከት ይህንን ሪፖርት አዘጋጅቷል፡፡

## 3.3 በምርመራ ሥራው ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

- ካለፉት ጥቂት ዓመታት ጀምሮ እስካሁን ሰመጉ ያለበት ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ፣ የሰው ኃይልና የምርመራ ቁሳቁስ እጥረት፣
- በአጠቃላይ በሐገሪቱ ያለው ፖለቲካዊ ሁኔታ በውጥረት የተሞላ በመሆኑና በተለይ በአሁኑ ወቅት በኦሮሚያ ክልል በተከሰተው ቀውስ ሳቢያ እንደልብ ተዘዋውሮ ለመሥራት አለመቻል፣ የመንግሥት የደኅንነትና የጸጥታ ኃይሎች ከፍተኛ ጫናና ክትትል ማድረጋቸው፣
- የሕዝቡ በከፍተኛ ፍርሐት ውስጥ መግባትና ማንንም ሰው ያለማመንና መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ያለመሆን ዋናዋናዎቹ ችግሮች ናቸው፡፡

ይሁንና ሰመጉ ከላይ የተጠቀሱትን አስቸጋሪ ሁኔታዎች በመቋቋም ምርመራውን ለማድረግና ይህንን ሪፖርት ለማዘጋጀት ችሏል፡፡

## 4. የመጀመርያው የተቃውሞ መነሻ

የመጀመርያው የተቃውሞ መነሻ ምዕራብ ሸዋ ዞን ደንዲ ወረዳ ጊንጪ ከተማ ነው፡፡ መነሻው በጊንጪ ከተማ የሚገኘውን የጊንጪ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ኳስ ሜዳ የጊንጪ ከተማ ከንቲባ፣ የወረዳው አስተዳዳሪና ሌሎችም ባለሥልጣናት ሸንሽነው ለግለሰቦች በመስጠታቸውና የተማሪዎቹን መጫወቻ ሜዳ የተረከቡት ግለሰቦች ሥፍራውን በማጠራቸው የጊንጪ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ድርጊቱን በመቃወም ኅዳር 02 ቀን 2008 ዓ.ም ተቃውሞ ማሰማታቸው ነው፡፡

የተማሪዎቹን ተቃውሞ ተከትሎ የጊንጪ ከተማ ከንቲባና ሌሎችም ባለሥልጣናት ግንባታው እንደሚቆም በመግለጽ ግንባታው እንዲቆም ተደረገ፡፡ ከዚህ በመቀጠል ለክፍለ ዘመናት ተጠብቆ የቆየው የጭልሞ ደን ለግለሰብ መሸጡን ተማሪዎች በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ አደረጉ፤ ሕዝቡም ሰልፉን ተቀላቅሎ ተቃውሞውን አሰማ፡፡ ከደኑ ይዞታ ሦስት የእግር ኳስ ሜዳ ያህል ስፋት ባለው መሬት ላይ የነበረ የሐበሻ ጥድ፣ የኮሶ እንዲሁም ሌሎች ሐገር በቀል ዕጽዋት ዛፎች በመጨፍጨፋቸው ተቃውሞው እየበረታ ሲሄድ የደኑ መጨፍጨፍ ቆሞ በነበረበት እንዲቆይ ተደረገ፡፡ ከዚህ በኋላ ‹‹የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ማስፋፋትን እንቃወማለን›› በማለት ተቃውሞው ቀጠለ፡፡ በዚህም ምክንያት መንግሥት በወሰደው የኃይል እርምጃ የሚከተሉት ሰዎች ተገድለዋል

## 5. በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች የደረሰው ጉዳት

### 5.1. ግድያ

1. **ሟች በቀለ ሌሊሳ፤** ዕድሜ 20 በደንዲ ወረዳ ሶምቦላሼኮ ቀበሌ ነዋሪ የነበረ ታኅሣሥ 3 ቀን 2008 ዓ.ም አስጎሪ ከተማ ከቀኑ 9 ሰዓት ላይ ብርሃኑ ኢፋ በተባለ የጸጥታ ዘርፍ ኃላፊ በጥይት ጭንቅላቱን ተመትቶ ተገድሏል። በ05/04/08 ጋትሮ ላፍቶ ቀበሌ ሥላሴ ቤተክርስትያን ተቀብሯል።



በቀለ ሌሊሳ

2. **ሟች ጫልሲሳ ጎንፋ፤** ዕድሜ 18 ደንዲ ወረዳ ሶምቦላሼኮ ቀበሌ ነዋሪ የነበረ በ03/04/08 አስጎሪ ከተማ 9 ሰዓት ላይ ብርሃኑ ኢፋ በተባለ የአስጎሪ ከተማ የጸጥታ ዘርፍ ኃላፊ ጭንቅላቱ ላይ በጥይት ተመትቶ ተገድሏል። በ05/04/08 ገትሮ ላፍቶ ቀበሌ ሥላሴ ቤተ ክርስትያን ከቀኑ በስምንት ሰዓት ቀብሩ ተፈጽሟል።



ጫልሲሳ ጎንፋ

3. **ሟች ሴፉ ቱራ፤** ዕድሜ 22 የቴክኒክና ሙያ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ በግል ሥራ የሚተዳደር፤ በ03/04/08 ከቀኑ 11 ሰዓት ላይ ጊንጪ መናኻሪያ አቅራቢያ በቀኝ በኩል ሽንጡ ላይ ተመትቶ ለሕክምና ወደ አዲስ አበባ እየተወሰደ ሳለ መንገድ ላይ ሕይወቱ አልፏል። ታኅሣሥ 05 ቀን 2008ዓ.ም ጊንጪ ከተማ በሚገኘው ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል።



ሴፉ ቱራ

4. **ሟች አስቻለው ወርቁ፤** ዕድሜው 22 የሆነ ጊንጪ መናኻሪያ ታኅሣሥ 05/2008 ዓ.ም ከቀኑ 11 ሰዓት ላይ በጥይት ተመትቶ ወደ አምቦ ሆስፒታል ለሕክምና ሲወሰድ መንገድ ላይ ሕይወቱ አልፏል። ታኅሣሥ 04/2008ዓ.ም ጋሬ ያሬራ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ተክለሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል።



አስቻለው ወርቁ

5. **ሟች ኩምሳ ጣፋ ጫላ**፤ *ዕድሜ 20 የወሎንኮሚ 01 ቀበሌ ነዋሪ ነበር*፤ በ05/04/08 *ዓ.ም የቀን ሥራ ላይ እንዳለ ወሎንኮሚ ፖሊስ ጣቢያ አካባቢ ከቀኑ* በ8 *ሰዓት ጀርባው ላይ በሁለት ጥይት ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል*። በ06/05/08 *ወሎንኮሚ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ከቀኑ* በ5 *ሰዓት የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል*።



ኩምሳ ጣፋ

6. **ሟች ሲሳይ በቀለ**፤ *ዕድሜ* 20 *ቀላም በርቱ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ነዋሪ የነበረ ሲሆን*፣ በ05/04/08 *ከቀኑ* በ8 *ሰዓት አካባቢ ወሎንኮሚ ፖሊስ ጣቢያ አካባቢ በመከላከያ ሠራዊት በተተኮሰ ጥይት ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል*። *የቀብር ሥርዓቱም* በ06/04/08 *ወሎንኮሚ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል*።

7. **ሟች ደበላ ነገራ**፤ *ዕድሜ* 32 በ04/04/08 *ዓ.ም ከቀኑ* 9 *ሰዓት ላይ በመከላከያ ሠራዊት አባላት በሦስት ጥይት እጁና ሆዱ ላይ ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል*። *የቀብሩ ሥነ ሥርዓት በጀልዱ ገብርኤል ቤተክርስቲያን* በ07/04/08 *ከቀኑ* በ8 *ሰዓት ተፈጽሟል*።



ደበላ ነገራ

8. **ሟች በቀለ ሰቦቃ**፤ በ27/03/2008 *ዓ.ም እንጪኒ ላይ በተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ተገድሎ* በ28/03/2008*ዓ.ም ሙገር ሩፋኤል ቤተክርስትያን የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ተፈጽሟል*።
9. **ሟች ዘውዴ ሥዩም** *ዕድሜ* 25 *አምቦ ኮሌጅ ተማሪ ነበር*። በ07/04/08 *ሙገር ከተማ ቀንና ሌሊት ሰልፍ በነበረበት ወቅት በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች በጥይት ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል*። *የቀብሩ ሥነ ሥርዓት* በ09/04/08 *በዳንሴ ማርያም ቤተክርስቲያን ተፈጽሟል*።
10. **ሟች በዳዳ ከበበ** በ07/04/08 *ዓ.ም ሙገር ከተማ ቀንና ሌሊት ሰላማዊ ሰልፍ በነበረበት ወቅት በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች በጥይት ተገድሎ* በ09/04/08 *ጉትቻ ማርያም ቤተክርስቲያን የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል*።
11. **ሟች ለማ መገርሳ** *የመኪና ረዳት የነበረ ሲሆን*፣ በ07/04/08 *ዓ.ም ሙገር ከተማ በተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ በታጣቂዎች ተገድሎ* በ09/04/08 *ጉትቻ ማርያም ቤተክርስቲያን የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል*።
12. **ሟች ግርማ ረጋሳ**፤ *ዕድሜ* 35 *አምቦ ከተማ ኢዶሊበን ቀበሌ ነዋሪ የነበረ ታኅሣሥ* 02 *ቀን* 2008 *ዓ.ም ከቀኑ* 9 *ሰዓት ላይ በመንግሥት ኃይሎች በሁለት ጥይት በዓይኑና አፉ አካባቢ ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል*። *የቀብሩ ሥነ ሥርዓት* በ04/04/2008*ዓ.ም ከቀኑ* በ6፡00 *በአምቦ እየሱስ ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል*።



ግርማ ረጋሳ

13. **ሟች ጫላ ድንቁሳ** *የአምቦ መሰናዶ ት/ቤት የ*11*ኛ ክፍል ተማሪ የነበረ* በ04/05/08 *ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች አምቦ መብራት ኃይል ግቢ ውስጥ ተገድሏል*። *ወዴሳ ቁሊት ቀበሌ* በ06/05/08*ዓ.ም የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል*።

14. **ሟች ታዳጊ ወጣት ተማሪ ዑልፋታ ኒግሳ፤** የሊበን ሜጫ ት/ቤት የአራተኛ ክፍል ተማሪና የ12 ዓመት ታዳጊ ነበረ። ታኅሣሥ 2 ቀን 2008 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች በአንገቱ ላይ ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል። በ04/04/08 ዓ.ም ቢርቢርሳ ቀበሌ የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል።



ዑልፋታ ኒግሳ

15. **ሟች ወረተ ዓለሙ፤** ዕድሜ 34 በ07/04/08ዓ.ም ሱሉልታ የግል ንብረቱ በነበረው ዳኒ ጋዜቦ ሆቴል እንዳለ የታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች የሆቴሉን አጥር ዘልለው በመግባት ሽንጡ ላይ በጥይት መትተውታል። አዲስ አበባ በራስ ደስታ ሆስፒታል ሕክምና ሲከታተል ቆይቶ በ15/04/08 ዓ.ም ሕይወቱ አልፏል። በ16/04/08 ከቀኑ 7 ሰዓት ሱሉልታ ከተማ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል።

16. **ተማሪ ፍቃዱ ግርማ ደበላ፤** ዕድሜ 16 ታኅሣሥ 29 ቀን 2008 ዓ.ም ጌዶ/ጨሊያ/ ላይ በተደረገ ሰላማዊ ሰልፍ በመንግሥት የታጠቁ ኃይሎች ተገድሏል።





ፍቃዱ ግርማ

17. **ተማሪ ደረጀ ጋዲሳ ታዬ፤** ዕድሜ 14 ታኅሣሥ 30 ቀን 2008 ዓ.ም ባብች ላይ በተደረገው የተቃውሞ ሰልፍ በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች በተተኮሰ ጥይት ተገድሏል።



ደረጀ ጋዲሳ

18. **ወጣት ታመነ ውብሸት ደምሰው፤** ዕድሜው 25፣ ነዋሪነቱ በጨሊያ ወረዳ ባቢች ከተማ ውስጥ ሲሆን 30/04/2008 ዓ.ም. ከቀኑ በግምት 8 ሰዓት አካባቢ ከአጋዚ ጦር አባላት በተተኮሰ ጥይት አንገቱ ላይ ተመትቶ ለህክምና ወደ ጌዶ ሆስፒታል በመሄድ ላይ እንዳለ በዚሁ እለት ህይወቱ አልፏል። የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ቤተሰብ፣ ወዳጅ ዘመድ በተገኙበት በ02/05/2008 ዓ.ም. በሙኞ ማሪያም ቤተክርስቲያን ተፈጽሟል።



ታመነ ውብሸት

19. **ሚች ታዳጊ ሻለማ ታሬሳ አትናሳ፤** ዕድሜው 13 ሲሆን ነዋሪነቱ በጨሊያ ወረዳ ቱሉ ማና በ12/05/2008 ዓ.ም. በጁማ ራሬ ወረዳ ፖሊስ አዛዥ በተተኮሰበት ጥይት አንገቱ ላይ ተመትቶ ህይወቱ ወዲያውኑ አልፎዋል። የቀብሩ ሥነ ሥርዓት በ13/05/2008 ዓ.ም. በጎባን ከተማ በፍንጣአ መንገድ በመካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን ከቀኑ በ8 ሰዓት ቤተሰቡና የአካባቢው ህዝብ በተገኙበት ተፈፅሟል።



ሻለማ ታሬሳ

20. **ሚች ተማሪ አበበ ለታ ጉደታ** እድሜ 15 ሽነን ቀበሌ 02 በመንግስት ታጣቂ ሀይሎች በ11/05/2008 ዓ.ም. በጥይት ተመትቶ ህይወቱ አልፎዋል።
21. **ሚች ወጣት አያንሳ ሂርቃታ** ዕድሜ 25 በ02/04/08ዓ.ም ወሊሶ ድሬዳሌቱ በመንግሥት ታጣቂ ኃይሎች ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል።
22. **ሚች ወጣት ታሪኩ አሰፋ፤** ዕድሜ 24 በ29/03/08 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ወሊሶ ከተማ ላይ ተገድሏል።
23. **ሚች ወጣት ሀብታሙ ተስፋዬ፤** ዕድሜ 28 በ02/04/08 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ወሊሶ ፊዳጎራ ላይ በጥይት ተገድሏል።
24. **ሚች ወጣት አያና መኮንን፤** ዕድሜ 25 በ02/04/08 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ወሊሶ ከተማ ላይ በጥይት ተገድሏል።
25. **ሚች ወጣት ሞረዳ ቀንዐ፤** ዕድሜ 23 በ29/03/08 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ወሊሶ ከተማ ላይ በጥይት ተገድሏል።
26. **ሚች ወጣት ዋቆ ሞረዳ፤** ዕድሜ 17 በ29/03/08 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ወሊሶ ከተማ ላይ በጥይት ተገድሏል።
27. **ሚች ወጣት ሌንጮ ሁንዴሳ፤** ዕድሜ 20 በ29/03/08 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ወሊሶ ከተማ ላይ በጥይት ተገድሏል።
28. **ሚች ወጣት ተሻለ ዑርጌሳ፤** ዕድሜ 22 በ03/04/2008 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ወንጪ ከተማ ላይ ተገድሏል።
29. **ሚች ወጣት ገላና በቃና** ዕድሜ 29፤በ28/03/2008 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ወንጭ ከተማ ላይ በጥይት ተገድሏል።
30. **ሚች ወጣት ብርሃኑ ዲንቃ** ዕድሜ 19፤ በ03/04/08 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ወንጭ ከተማ ላይ በጥይት ተገድሏል።
31. **ሚች ወጣት ሰርቤሳ ከበደ** ዕድሜ 23፤ በ28/03/08 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ወንጭ ከተማ ላይ በጥይት ተገድሏል።
32. **ሚች ወጣት ሰርቤሳ ሰርኔሳ** ዕድሜ 19፤ በ03/04/2008 ዓ.ም በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች ወንጭ ከተማ ላይ በጥይት ተገድሏል።
33. **ሚች ደረጀ ወርቅነህ** ዕድሜ 78፤ በ03/04/08 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ወንጭ ከተማ ላይ በጥይት ተገድሏል።
34. **ሚች ከበደ ታደሰ** ዕድሜ 65፤ በ03/04/08 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ወንጭ ከተማ ላይ ተገድሏል።
35. **ሚች ወጣት ኃይሌ ዱባለ** ዕድሜ 30፤ በ28/03/08 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ወንጭ ከተማ ላይ ተገድሏል።
36. **ሚች ኤቢሳ ጉቱ፤** በ27/03/08 ዓ.ም ፊንጫ ሽለቆ በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ተገድሏል።



ኤቢሳ ጉቱ

37. **ሟች ወጣት ዋቁማ ቶሊሳ** *ዕድሜ* 18፤ በ04/04/8 ዓ.ም ገበቴ ከተማ በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ተገድሏል፡፡ የቀብሩ ሥነ ሥርዓት በ05/04/08 በገበቴ መካነ እየሱስ ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል፡፡



ዋቁማ ቶሊሳ

38. **ሟች ወ/ሮ ሻሽቱ ፍርዳሳ**፤ በ07/04/08 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ቀረዋትዬ ላይ ተገድለዋል፡፡ የቀብራቸው ሥርዓትም በቀረዋትዬ መካነ እየሱስ ተፈጽሟል፡፡
39. **ሟች አቶ ቶሌሳ ሌሊሳ**፤ በ07/04/08 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ቀረ ዋትዬ ላይ ተገድለዋል፡፡
40. **ሟች ወጣት ገበየሁ አምሳሉ ቱሉ**፤ በሳሲጋ ወረዳ በታጣቂዎች በ07/04/2008ዓ.ም ተገድሏል፡፡

41. **ሟች ተማሪ ካራሳ ጫላ** *ዕድሜ* 17፤ በ23/03/08 ዓ.ም በመንግሥት ታጣቂ ኃይሎች ጉሊሶ (ጨሊያ) ከተማ ግድያ ተፈጽሞበታል፡፡



ካራሳ ጫላ

42. **ሟች ተማሪ ጉቱ አበራ** *ዕድሜ* 20፤ በ22/03/08 ዓ.ም በመንግሥት ታጣቂ ኃይሎች ጉሊሶ (ጨሊያ) ከተማ ግድያ ተፈጽሞበታል፡፡



ጉቱ አበራ

43. **ሟች ተማሪ ሉጫ ገመቹ** *ዕድሜ* 18፤ በ30/03/2008 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች እናንጎ (ላሎ ወንጆ) ላይ ግድያ ተፈጽሞበታል፡፡
44. **ሟች ወጣት አያና በንቲ** *ዕድሜ* 17፤ በ30/03/2008 ዓ.ም (ላሎወንጆ) ላይ ግድያ ተፈጽሞበታል፡፡

45. **ሟች ወጣት ዓላዛር መርጋ** *ዕድሜ* 20፤ በ30/03/2008 ዓ.ም በመንግሥት የታጠቁ ኃይሎች እናንጎ ከተማ ላይ ግድያ ተፈጽሞበታል፡፡



ዓላዛር መርጋ

46. **ሟች ጥላሁን ሙላታ** ዕድሜ 60፤ በ06/04/08ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ደንቢዶሎ ከተማ 07 ቀበሌ ግድያ ተፈጽሞባቸዋል።



ጥላሁን ሙላታ

47. **ሟች ወ/ሮ ሲረኔ ጉደታ** ዕድሜ 45፤ በ04/04/08ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ጫንቃ ላይ ግድያ ተፈጽሞባቸዋል።



ሲረኔ ጉደታ

48. **ሟች ወጣት እሸቱ ፈዬሳ** ዕድሜ 28፤ በ04/04/08 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ጫንቃ ላይ ግድያ ተፈጽሞባቸዋል። እሸቱ የሟች ወ/ሮ ሲረኒ ጉደታ ልጅ ነው ።



እሸቱ ፈዬሳ

49. **ሟች ወጣት ቀጀላ ዮሐንስ** ዕድሜ 16፤ በ04/04/08 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ጫንቃ ጊምቢ ላይ (ዋሎየሱስ) ግድያ ተፈጽሞበታል።
50. **ሟች በሪ ሰዒድ ዐሊ** ዕድሜ 27፤ በ03/05/08 ዓ.ም መሰላ ወረዳ ጉቤቲ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር በተደረገ የሕዝብ ሰላማዊ ሰልፍ በመንግሥት የታጠቁ ኃይሎች ተገድሏል።
51. **ሟች ሁሴን ዳዊ አመድ** ዕድሜ 30፤ በ27/04/08 ዓ.ም በመንግሥት የታጠቁ ኃይሎች መሰላ ከተማ ላይ በጥይት ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል።



ሁሴን ዳዊ

52. **ሟች ገመቹ ጥላሁን** ዕድሜ 24፤ በ06/04/08 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ነጆ ከተማ በጥይት ተመትቶ ሞቷል።



ገመቹ ጥላሁን

53. **ሟች ወጣት ምስራ ሐጂ ናቦ ወጤሳ**፤ ዕድሜ 14፤ በ01/04/08 ዓ.ም ከቀኑ 7 ሰዓት ላይ በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች አዳባ ከተማ ቀበሌ 02 ጭንቅላቷ ላይ በጥይት ተመትታ ሕይወቷ አልፏል።

54. **ሟች ወጣት ሁሴን ሃጅ ደሱ**፤ ዕድሜ 33፤ አዳባ ከተማ ቀበሌ 02 ነዋሪ የነበረ ወደ መስጊድ ለመስገድ ሲሄድ በ01/04/08 ዓ.ም በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች በጥይት ሆዱ ላይ ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል።




ሁሴን ሃጅ

55. **ሟች ነስረዲን መሐመድ ወሊ**፤ ዕድሜ 38፤ በ01/04/08 ዓ.ም ከቀኑ 6 ሰዓት በመንግሥት የታጠቁ ኃይሎች አዳባ ከተማ 01 ቀበሌ በጥይት በጆርባውና በታፋው ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል።



ነስረዲን መሐመድ

56. **ሟች ተማሪ ሙራድ አብዲ**፤ ዕድሜ 19፤ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ የነበረ በ26/03/08ዓ.ም ከቀኑ በ5 ሰዓት ሀሮማያ ከተማ በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ቀኝ ጎኑ ላይ ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል፡፡ በ27/03/08ዓ.ም በባቴ ወረዳ በሙስሊም መካነ መቃብር የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል፡፡

ሙራድ አብዲ



57. **ሟች ጸጋዬ አበበ**፤ ዕድሜ 15፤ በ03/04/08 ዓ.ም በተደረገ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ በመንግሥት የታጠቁ ኃይሎች ጀልዱ ከተማ ላይ ተገድሎ በጀልዱ የፕሮቴስታንት መካነ መቃብር የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል፡፡

58. **ሟች ብርቱካን በዳዳ**፤ በጀልዱ ወረዳ ኮሉ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ነዋሪ የነበረች በ03/04/08 ዓ.ም በሰላማዊ ሰልፉ ላይ በመንግሥት የታጠቁ ኃይሎች ተገድላ ጀልዱ ከተማ በሚገኘው የፕሮቴስታንት መካነ መቃብር የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል፡፡

59. **ሟች ደጀኔ ኢብሳ**፤ ጀልዱ ወረዳ ኮሉ ገላን ቀበሌ ዕድሜ 38፤ በ03/04/08ዓ.ም ከምሽቱ 2 ሰዓት ላይ በዳዳ ነገሪ ሁንዴ በተባለ የቀበሌው ታጣቂ ተገድሏል፡፡ ኮሉ ገላን ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል፡፡

60. **ሟች ለሜሳ ኮኩና**፤ ጀልዱ ከተማ በ04/04/08 ዓ.ም በተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ በመንግሥት የታጠቁ ኃይሎች ተገድሎ ጦቢ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል፡፡

61. **ሟች ባይሳ ወጋ**፤ ጀልዱ ከተማ በ04/04/08 ዓ.ም በተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ በመንግሥት የታጠቁ ኃይሎች ተገድሎ ጦቢ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል፡፡

62. **ሟች ተማሪ ሳምሶን ከተማ** በቀለ፤ የ5ኛ ዓመት የምሕንድስና ተማሪ የነበረ ታኅሣሥ 30 ቀን 2008 ዓ.ም ከምሽቱ 4 ሰዓት ላይ በተነሣው የተማሪዎች ተቃውሞ መዳ ወላቡ ዩኒቨርሲቲ መኝታ ክፍል ውስጥ ሞቶ የተገኘና ወላጆቹ ወደሚገኙበት ድሬዳዋ ከተማ አስከሬኑ ተልኮ ድሬዳዋ ከተማ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን በ03/05/08 ዓ.ም የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል፡፡

ሳምሶን ከተማ



63. **ሟች ባይሳ ገደፋ**፤ ዕድሜ 28 በጉልበት ሥራ ይተዳደር የነበረ ታኅሣሥ 01/2008 በግንደበረት ወረዳ አቡና ከተማ በኦሮሚያ ፖሊስ ጀርባውን በጥይት ተመትቶ የተገደለ፡፡ ታኅሣሥ 03 ቀን 2008ዓ.ም ቀብሩ በገብረ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል፡፡

ባይሳ ገደፋ



64. **ሟች ታደሰ ዳባ ዕድሜ** 25፤ በ04/04/08 በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች በጥይት ከጀርባው ተመትቶ የተገደለ። ወልዳ መሠረተ ክርስቶስ መካነ መቃብር ተቀብሯል።

ታደሰ ዳባ



65. **ሟች እናጋው ኃይሉ** ዕድሜ 25፤ ታኅሣሥ 02/2008 በካቺሲ ከተማ በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች በጥይት ግንባሩን ተመትቶ ታኅሣሥ 03/2008 ሕይወቱ አልፏል። ታኅሣሥ 04/2008 ዓ.ም ወልዳ መካና ደቤ መካነ መቃብር የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል።

እናጋው ኃይሉ



66. **ሟች ያለው ደምሴ**፤ የ32 ዓመት ወጣት ነው። በኤልፈታ ወረዳ በኬ ከተማ ታኅሣሥ 02/2008 ዓ.ም በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች ከኋላው በኩል ቀኝ ኩላሊቱን በጥይት ተመትቶ በዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ሕክምና ቢከታተልም በ04/04/08 ሕይወቱ አልፏል። ሥርዓተ ቀብሩም በ07/04/08 በኤልፈታ ወረዳ በኬ አቦ ቤተክርስቲያን ተፈጽሟል።

ያለው ደምሴ



67. **ወጣት ፍቃዱ ድሪባ** እድሜው 17 ሲሆን ነዋሪነቱ በአመያ ከተማ ትርቲራ ቀበሌ ውስጥ ሲሆን ታኅሣሥ 04/2008 ዓ.ም በመንግሥት ታጣቂ ኃይሎች በተተኮሰ ጥይት ግንባሩ ላይ ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል። ወላጆቹ 100 ብር ከፍለው አስከሬኑን እንዲረከቡ ተደርገዋል። የቀብሩ ሥነ ሥርዓትም ታኅሣሥ 05/2008 ዓ.ም. ትርትራ ቤተክርስቲያን ቤተሰብ እና ጓደኞቹ በተገኙበት ተፈጽሟል።

ፍቃዱ ድሪባ



68. **ወጣት ጉደታ ባይሳ** እድሜው 19 ነዋሪነቱ ባቢች ከተማ ውስጥ ሲሆን ህዳር 30/2008 ዓ.ም መንገድ እየሄደ ባለበት ወቅት ከአጋዚ ጦር በተተኮሰ ጥይት ኩላሊቱ አካባቢ ተመትቶ ህይወቱ ወዲያውኑ አልፏል። የቀብሩ ሥነ ሥርዓትም ታህሳስ 01/2008 ዓ.ም በባቢች ከተማ ቱሉ ባጀ መካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን ቤተሰቡ፣ ጓደኞቹና የአካባቢው ሰው በተገኙበት ተፈጽሟል።

ጉደታ ባይሳ



69. **ወጣት ወንዱ ኬነሳ** እድሜው 26 ሲሆን ነዋሪነቱ በአመያ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ ሲሆን ታህሳስ 04/2008 ዓ.ም. ከቀኑ 5 ሰዓት አካባቢ አመያ ወረዳ 01 ቀበሌ ውስጥ ከአጋዚ ጦር በተተኮሰበት ጥይት ጭንቅላቱ ላይ ተመትቶ ወዲያውኑ ህይወቱ አልፏል፡፡ የቀብሩ ሥነ ሥርዓትም ታህሳስ 05/2008 ዓ.ም. ቤተሰቡና ወዳጆቹ በተገኙበት በአመያ ማርያም ቤተክርስቲያን ተፈጽሟል፡፡



ወንዱ ኬነሳ

70. **ወጣት ግርማ እሸቱ** እድሜው 26 ሲሆን ነዋሪነቱ በአመያ ከተማ ትርትራ ቀበሌ ነዋሪ ነው፡፡ ታህሳስ 04/2008 ዓ.ም. በግምት ከቀኑ 5 ሰዓት አካባቢ ከአጋዚ ጦር በተተኮሰበት ጥይት ተመትቶ ህይወቱ አልፏል፡፡ የቀብሩ ሥነ ሥርዓትም ቤተሰቡና ወዳጆቹ በተገኙበት ታህሳስ 05/2008 ዓ.ም. በአመያ ማርያም ቤተክርስቲያን ተፈጽሟል፡፡



ግርማ እሸቱ

71. **ወጣት አያንሳ ማዴባ** እድሜው 18 ሲሆን ነዋሪነቱ በወሊሶ ከተማ ውስጥ ሲሆን ህዳር 29/2008 ዓ.ም. ከመከላከያ ሰራዊት አባል በተተኮሰበት ጥይት ህይወቱ አልፏል፡፡
72. **ወጣት ደረጀ ወርቁ** እድሜው 26 ሲሆን ነዋሪነቱ በአመያ ከተማ ውስጥ ሲሆን ከአጋዚ ጦር በተተኮሰበት ጥይት በ04/04/2008 ዓ.ም. ሕይወቱ አልፏል፡፡
73. **ወጣት ታየ ዱፌራ** እድሜው 24 ሲሆን ነዋሪነቱ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት አመያ ከተማ ውስጥ ሲሆን ከአጋዚ ጦር በተተኮሰበት ጥይት በ04/04/2008 ዓ.ም. ሕይወቱ አልፏል፡፡
74. **ወጣት አበበ ቡሌ** እድሜው 25 ሲሆን በግል ስራ የሚተዳደር የአመያ ከተማ ነዋሪ ነው፡፡ ከአጋዚ ጦር በተተኮሰበት ጥይት በ04/04/2008 ዓ.ም. ሕይወቱ አልፏል፡፡
75. **ወጣት ረቡማ ጌራ** እድሜው 26 ሲሆን በግል ስራ የሚተዳደር አመያ ከተማ ነዋሪ ነው፡፡ ከአጋዚ ጦር በተተኮሰበት ጥይት በ05/04/2008 ዓ.ም. ሕይወቱ አልፏል፡፡
76. **አቶ በሊ ኩርኩራ** ዕድሜው 29፣ ነዋሪነቱም በአመያ ከተማ ውስጥ ሲሆን ከአጋዚ ጦር በተተኮሰበት ጥይት በ05/04/2008 ዓ.ም. ሕይወቱ አልፏል፡፡
77. **አቶ ተፈራ ዳንጊያ** እድሜው 30፣ ነዋሪነቱ በአመያ ከተማ ውስጥ ሲሆን ከአጋዚ ጦር በተተኮሰበት ጥይት በ05/04/2008 ዓ.ም. ሕይወቱ አልፏል፡፡
78. **ሟች ኩመላ እሸቴ** ዕድሜው 19፣ በአመያ ወረዳ 01 ቀበሌ በ04/04/08ዓ.ም በመከላከያ ሠራዊት አባላት በተተኮሰ ጥይት ተገድሏል፡፡
79. **ሟች ብርሃኑ በጅጋ** በ04/04/2008 ዓ.ም ጀልዱ ወረዳ በተደረገ ሰላማዊ ሰልፍ በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ተገድሏል፡፡
80. **ሟች መገርሣ በቺ** በ04/04/08 ዓ.ም ጀልዱ ወረዳ በተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ተገድሏል፡፡
81. **ሟች በቀለ ቶምሳ** በ04/04/08 ዓ.ም ጀልዱ ወረዳ በተደረገ ሰላማዊ ሰልፍ በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ተገድሏል፡፡
82. **ሟች ምክትል ኢንስፔክተር ዲባባ ወየሳ** በ04/04/08 ዓ.ም በተደረገ የሕዝብ ሰላማዊ ሰልፍ ግንደበረት ወረዳ አቡና ከተማ ሕይወቱ አልፏል፡፡
83. **ሟች ሳጅን ታደሰ ጀምበሬ** በ04/04/08 ዓ.ም በተደረገ የሕዝብ ሰላማዊ ሰልፍ ግንደበረት ወረዳ አቡና ከተማ ሕይወቱ አልፏል፡፡ የቀብር ሥርዓቱ ጀልዱ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ቤተሰቦቹ በተገኙበት ተፈጽሟል፡፡
84. **ዋና ሳጅን ወገኔ ደበሎ** በ04/04/08 ዓ.ም በተደረገ የሕዝብ ሰላማዊ ሰልፍ ግንደበረት ወረዳ አቡና ከተማ ሕይወቱ አልፏል፡፡
85. **ሟች አብደታ ኦሌንሳ** ዕድሜው 25 የሆነ የአምቦ ከተማ ነዋሪ ከሐምሌ ወር 2007 ዓ.ም ጀምሮ በቂሊንጦ እሥር ቤት ታሥሮ አዲስ አበባ አቤል ሆስፒታል ሕክምና ሲደረግለት ቆይቶ ሕይወቱ

አልፏል፡፡ አስከሬኑ ወደ ትውልድ ሥፍራው አምቦ ተወስዶ ወደ ቀብር ሲሄድ በተደረገ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ ሁለት ወጣቶች ተገድለዋል፡፡

86. **ሟች ደበላ ጣፋ ሮቢ** በ22/03/08ዓ.ም ሱሉልታ ከተማ በፌደራል ፖሊስ በጥይት ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል፡፡
87. **ሟች ደጀኔ ሰርቤሳ** በ23/03/08 ዓ.ም ቶሌ ከተማ በፌደራል ፖሊስ በተተኮሰ ጥይት ተገድሏል፡፡
88. **ሟች ባይሳ በዳሳ** በ29/03/08 ዓ.ም ባኮ በመንግሥት የታጠቁ ኃይሎች በጥይት ተገድሏል፡፡
89. **ሟች ጉደታ ባይሳ ጎበና** በ30/03/08 ዓ.ም ባቢች ላይ በመንግሥት ታጣቂ ኃይሎች ተገድሏል፡፡
90. **ሟች ባይሳ ታደሰ** በ30/03/08 ዓ.ም አቡነግንደበረት በመንግሥት ታጣቂ ኃይሎች ተገድሏል፡፡
91. **ሟች ቡኢ ዳባ** በ30/03/08ዓ.ም አቡነግንደበረት በመንግሥት ታጣቂ ኃይሎች ተገድሏል፡፡
92. **ሟች ሻቢ ዳባ** በ30/03/08ዓ.ም አቡነግንደበረት በመንግሥት ታጣቂ ኃይሎች ተገድሏል፡፡
93. **ሟች በንቲ ዱጉማ** በ30/03/08ዓ.ም ላሎአሳምቢ በመንግሥት ታጣቂ ኃይሎች ተገድሏል፡፡
94. **ሟች ጋሬዶ ቶሎሳ** በ02/04/08ዓ.ም ወሊሶ ጉራራ ቦኮ በመንግሥት ታጣቂ ኃይሎች ተገድሏል፡፡
95. **ሟች ቦሩ ጉተማ** በ03/04/08 አመያ ወረዳ ኩኖ ቁሊት በመንግሥት ታጣቂ ኃይሎች ተገድሏል፡፡

## 5.2. በጥይት ማቁሰል፣ ድብደባና ማሠቃየት

በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 18(1) ላይ ‹‹ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው›› ተብሎ የተደነገገውንና በዓለም አቀፉ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 5 ‹‹ማንም ሰው የማሠቃየት ድርጊት ሊፈጸምበት ወይም በጭካኔና ኢ ሰብዓዊ በሆነ መንገድ ሊጉላላ ወይም ሊዋረድ ወይም ሊቀጣ አይችልም›› በማለት የተደነገገውን በመጣስ ከዚህ በታች ስማቸው በተጠቀሰ ሰዎች ላይ ድብደባና ማሠቃየት ተፈጽሟል፡፡

1. **ወጣት ያደሳ ሞረዳ**፤ ዕድሜ 14፤ በ29/03/2008 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ወሊሶ ከተማ የቀኝ ታፋው ላይ በጥይት ተመትቶ በሕክምና ላይ ይገኛል፡፡
2. **ወጣት ነብሶ ገለታ**፤ ዕድሜ 15፤ በ29/03/2008 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ወሊሶ ከተማ ሆዱ ላይ በጥይት ተመትቶ በሕክምና ላይ ይገኛል፡፡
3. **ወጣት ሙለታ አያንሳ**፤ ዕድሜ 19፤ በ29/03/2008 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ወሊሶ ከተማ ቀኝ ትከሻው ላይ በጥይት ተመትቶ በሕክምና ላይ ይገኛል፡፡
4. **ወጣት ለማ ተረፈ**፤ ዕድሜ 18፤ በ28/03/2008 ዓ.ም በመንግሥት ታጣቂ ኃይሎች ወንጭ ከተማ ላይ ግራ እግሩን ከጉልበቱ በላይ በጥይት ተመትቶ በሕክምና ላይ ይገኛል፡፡
5. **ተማሪ ሰሎሞን ሞገስ**፤ ዕድሜ 19፤ በ28/03/2008 ዓ.ም በመንግሥት ታጣቂ ኃይሎች ወንጭ ከተማ ጉልበቱ ላይ በጥይት ተመትቶ በሕክምና ላይ ይገኛል፡፡
6. **አቶ ከቤ ዋቅጅራ**፤ ዕድሜ 45፤ በ27/03/2008 ዓ.ም ከቀኑ 7 ሰዓት በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ሜታሮቢ /ሽኖ/ ከተማ በጥይት ተመትቶ በሕክምና ላይ ይገኛል፡፡
7. **አቶ ቡሉ አበራ**፤ ዕድሜ 25፤ በ06/04/08 ዓ.ም በመንግሥት ታጣቂ ኃይሎች ደንቢ ዶሎ ከተማ 07 ቀበሌ በሁለት ጥይት እግሩንና እጁን ተመትቶ በሕክምና ላይ ይገኛል፡፡
8. **ተማሪ ሁንዴሳ አያላ**፤ ዕድሜ 20፤ በ04/04/08 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ደንቢዶሎ ቀበሌ 03 በጥይት ግራ ትከሻው ለይ ተመትቶ በሕክምና ላይ ይገኛል፡፡

ሁንዴሳ አያላ



9. **ወጣት ሌሊሳ ፍቅሬ፤** ዕድሜ 26፤ በ04/04/08 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ደንቢ ዶሎ ከተማ ቀበሌ 04 በሽንጡ ላይ በጥይት ተመትቶ በሕክምና ላይ ይገኛል፡፡



ሌሊሳ ፍቅሬ

10. **ተማሪ ሐዊ ያደታ፤** ዕድሜ 17፤ በ04/04/08 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ደንቢ.ዶሎ ከተማ በጥይት ግራ እግሯ ላይ ከጉልበቷ በታች ተመትታ ደንቢ ዶሎ ሆስፒታል በሕክምና ላይ ትገኛለች፡፡



ሐዊ ያደታ

11. **ተማሪ ሌሊሳ በንቲ፤** ዕድሜ 18፤ በ22/03/08 ዓ.ም በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ጉሉሶ (ጨልያ) ከተማ በትከሻው ላይ በጥይት ተመትቶ ደንቢ ዶሎ ሆስፒታል በሕክምና ላይ ይገኛል፡፡



ሌሊሳ በንተ

12. **ተማሪ ዋቅጅራ ጊዲሳ፤** ዕድሜ 17፤ የ10ኛ ክፍል ተማሪ በ27/03/08 ዓ.ም ከቀኑ 9 ሰዓት ላይ ፊንጫ ሸለቆ ቀበሌ በተማሪዎች የተቃውሞ ሰልፍ በተደረገበት ወቅት በፌዴራል ፖሊሶች በተተኮሰ ጥይት የቀኝ እግሩ ባቱ ላይ ተመትቶ በሕክምና ላይ ይገኛል፡፡



ዋቅጅራ ጊዲሳ

13. **ተማሪ መልኬ ከበደ**፤ ዕድሜዋ 17፤ የ6ኛ ክፍል ተማሪ በ27/03/08ዓ.ም 11 ሰዓት ላይ በፊንጫ ሸለቆ ኅብረተሰቡ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ አድርጎ ነበር፡፡ተማሪ መልኬ በሰልፉ ላይ ተሳታፊ አልነበረችም፡፡ በመንገድ ስትጓዝ በፌዴራል ፖሊሶች በተተኮሰ ጥይት ቀኝ እግሯ ላይ ከጉልበቷ በታች ተመትታ አዲስ አበባ ቤቴል ሆስፒታል በሕክምና ላይ ትገኛለች፡፡




መልኬ ከበደ

14. **ወጣት ሮባ ታዬቦሩ**፤ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን ጉድሩ ወረዳ ገበቴ 01 ቀበሌ በ04/04/2008ዓ.ም የአካባቢው ሕዝብ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ በሚያደርግበት ጊዜ የታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች ወደሚሠራበት የግል ጋራዥ በመሄድ ግራ እግሩን ባቱ ላይ በመምታት አቁስለውት ሕክምና በመከታተል ላይ ይገኛል፡፡



ሮባ ታዬቦሩ

15. **ታዳጊ ቱጂ ሀሰን አሊይ**፤ ዕድሜ13፤ በ27/04/2008ዓ.ም በመንግሥት የታጠቁ ኃይሎች መሰላ ከተማ በጥይት ግራ ደረቱን ተመትቶ በሕክምና ላይ ይገኛል፡፡



ቱጂ ሀሰን

16. **መሀመድ አመድ አመዲን**፤ ዕድሜ 21፤ በ27/04/08 ዓ.ም በመንግሥት የታጠቁ ኃይሎች መሰላ ከተማ በጥይት ግራ ደረቱ ላይ ተመትቶ በሕክምና ላይ ይገኛል።



መሀመድ አመድ

17. **መሀመድ ዩሱፍ ዑመሬ**፤ ዕድሜ 27፤ በ27/04/08 ዓ.ም በመንግሥት የታጠቁ ኃይሎች መሰላ ከተማ በጥይት ቀኝ እግሩን ተመትቶ በሕክምና ላይ ይገኛል።



መሀመድ ዩሱፍ

18. **ኢብራሂም ዑመር አብደላ**፤ ዕድሜ 20፤ በ27/04/08 ዓ.ም በመንግሥት የታጠቁ ኃይሎች መሰላ ከተማ በጥይት ሆዱ ላይ ተመትቶ በሕክምና ላይ ይገኛል።



ኢብራሂም ዑመር

19. **አብደላ ሱሌማን አህመድ፣** ዕድሜ 21፤ በ27/04/08 ዓ.ም በመንግሥት የታጠቁ ኃይሎች መሰላ ከተማ በጥይት ሁለት ታፋውን ተመትቶ በሕክምና ላይ ይገኛል።

አብደላ ሱሌማን



20. **ታዳጊ ጉተማ ኢብራሂም ዑመሬ**፤ ዕድሜ 11፤ በ27/04/08 ዓ.ም በመንግሥት የታጠቁ ኃይሎች መሰላ ከተማ በጥይት ቀኝ ታፋውን ተመትቶ በሕክምና ላይ ይገኛል።

ጉተማ ኢብራሃም



21. **አህመድ ዑመር አብደላ** ዕድሜ 25፤ በ27/04/08 ዓ.ም በመንግሥት የታጠቁ ኃይሎች መሰላ ከተማ ቀኝ እጁን በሳንጃ ተወግቶ በሕክምና ላይ ይገኛል።

አህመድ ዑመር



22. **ተማሪ አብድ ኢመሱ**፤ ዕድሜ 14፤ በ05/04/08 ዓ.ም በመንግሥት ታጣቂ ኃይሎች አይራ ከተማ በጥይት ግራ እግሩ ላይ ተመትቶ በሕክምና ላይ ይገኛል።

አብድ ኢመሱ



23. **ወጣት ደበላ ታሲሳ**፤ ዕድሜ 22፤ በ05/04/08 ዓ.ም በመንግሥት ታጣቂ ኃይሎች አይራ ከተማ አንገቱን በግራ በኩል ተመትቶ በሕክምና ላይ ይገኛል።



ደበላ ታሲሳ

24. **ሕጻን ቀነኒ መኮንን** ዕድሜ 9 የሁለተኛ ክፍል ተማሪ፤ በ05/04/08 ዓ.ም በመንግሥት የታጠቁ ኃይሎች አይራ ከተማ ቀኝ እግሩ ላይ በጥይት ተመትቶ በሕክምና ላይ ይገኛል።

25. **ወጣት ዑመር ቃሲም** ፤ ዕድሜ 17፤ በ01/04/08 ዓ.ም በመንግሥት የታጠቁ ኃይሎች በአዳባ ከተማ 02 ቀበሌ በጥይት ከዕምብርቱ በታች ተመትቶ በሕክምና ላይ ይገኛል።



Saafa — Umrii
ጾታ ዕድሜ
Lammummaa
ዜግነት
Godina — Aanaa
ዞን ወረዳ
Ganda — lakk Bilbilaa
ቀበሌ የስልክ ቁጥር
Lakk Bil M/B
የት/ቤቱ ስልክ 0226630006
Guyyaa wayagaa Eenyummaa
1.Baya2008 —kutaa— dayee
2.Baya2009— kutaa—dayee
3.Baya2010—kutaa—dayee
Hogganaa ManaBarnoota
የተ/ቤቱ ርዕሰ መምህር
Maqaa
Mallattoo
ፊርማ
ቁጥር

ዑመር ቃሲም

26. **ገላና ዋቅቶሌ**፤ ዕድሜ 21፤ በ06/04/2008 ዓ.ም በመንግሥት የታጠቁ ኃይሎች ነጆ ከተማ እጁ ላይ ሁለት ቦታ ተመትቶ በሕክምና ላይ ይገኛል።




ገላና ዋቅቶሌ

27. **ወጣት ጳውሎስ ገመቹ**፤ በ12/04/08 ዓ.ም ከምሽቱ 3 ሰዓት ፊንጫ ከተማ 02 ቀበሌ በታጠቁ የመንግሥት ኃይሎች በመኪና ተወስዶ ከፍተኛ ድብደባ ተፈጽሞበታል። በእግሮቹ ላይ ከባድ ጉዳት ስለደረሰበት በሕክምና ላይ ይገኛል።



ጳውሎስ ገመቹ

28. **ፍቅሩ ነዲ ወዬሳ**፤ ዕድሜ 16፤ በ01/04/08 ዓ.ም ግንደበረት ወረዳ አቡና ከተማ በኦሮሚያ ፖሊስ አባላት ቀኝ ጎኑ ከመቀመጫው ከፍ ብሎ በጥይት ተመትቶ በሕክምና ላይ ይገኛል፡፡
29. **ሻምበል ዳባ ኢቲቻ** ዕድሜ 16፤ በ01/04/08 ዓ.ም ግንደበረት ወረዳ አቡና ከተማ በኦሮሚያ ፖሊስ አባላት ሆዱ ላይ በጥይት ተመትቶ በሕክምና ላይ ይገኛል፡፡
30. **አቶ ጸጥአርጋቸው ዝክሩ** እድሜው 20 ባቢች ከተማ ላይ ህዳር 30/2008 ዓ.ም. ከቀኑ 8፡30 አካባቢ በኣጋዚ ጦር በተተኮሰ ጥይት ጀርባውን ተመቷል፡፡



ጸጥአርጋቸው ዝክሩ

31. **ወ/ሮ ሌሊሴ ቀና ጡሪ**፣ እድሜ 35፣ ታህሳስ 5/2008 ዓ.ም. ገበያ ውለው ወደ ቤታቸው ሲመለሱ መንገድ ዳር ላይ ከአጋዚ ጦር በተተኮሰ ጥይት አንገታቸው ላይ ተመተው በጽኑ ቆስለዋል፡፡



ሌሊሴ ቀና

32. **ተማሪ ጊቢቱ ኢማና ኢቲቻ**፣ እድሜ 19 የ8ኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን ህዳር 30/2008 ዓ.ም. በግምት 8፡00 ሰዓት ላይ ከአጋዚ ጦር ሠራዊት በተተኮሰ ጥይት ባቢች ከተማ ቀበሌ 01 መናህሪያ አካባቢ የቆሰለች፡፡



ጊቢቱ ኢማና

33. **ተማሪ ፊይሳ ተሰማ**፣ እድሜው 16፣ የሰባተኛ ክፍል ተማሪ ሲሆን በኦሮሚያ ጨሊያ ጌዶ ከተማ ፍርቲኖ አካባቢ በ30/03/2008 ዓ.ም. ከቀኑ በግምት 4 ሰዓት አካባቢ በተተኮሰበት ጥይት የቀኝ መንጋጋውን የተመታ፣ በዚህም 3 ጥርሶቹ ላይ ጉዳት ደርሶበታል፡፡

34. **ተማሪ ጫላ ተሾመ ልኬሳ፣** እድሜው 17፣ የሰባተኛ ክፍል ተማሪ ሲሆን ነዋሪነቱ በኦሮሚያ ክልል ጨሊያ ወረዳ ባቢች ከተማ 01 ቀበሌ ነው፡፡ በ30/03/2008 ዓ.ም. ከቀኑ በግምት 8 ሰዓት አካባቢ ባቢች ከተማ መናህሪያው አካባቢ ከአጋዚ ጦር በተተኮሰበት ጥይት ሆዱ ላይ ተመትቶ በጌድኦ ሆስፒታል ከዚያም ወደ አዲስ አበባ ሪፈራል ተጽፎለት በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ህክምና ወስዷል፡፡ ይሁንና አሁንም ሙሉ ለሙሉ ጤንነት እንደማይሰማው ለሰመጉ ባለሙያዎች አስረድቷል፡፡



ጫላ ተሾመ

35. **ጌታቸው ተስፋ፣** ዕድሜው 30፣ በግብርና ስራ የሚተዳደር በ04/04/2008 ዓ.ም. በግምት ከጠዋቱ 4:30 ሰዓት አካባቢ አመያ ከተማ ውስጥ ከመከላከያ ሰራዊት በተተኮሰ ጥይት የግራ ትከሻው ላይ ተመትቶ ወሊሶ ቅዱስ ሉቃስ ሆስፒታል ህክምና ተከታትሎ ወጥቷል፡፡

36. **ወጣት ደበላ ተፈሪ፣** ደምቢዶሎ ከተማ ቀበሌ 04 ነዋሪ፤ በጥይት ደረቱ ላይ የተመታ፡፡



ደበላ ተፈሪ

37. **ጉልማ መንገሻ**፤ ጥር 11 ቀን 2008 ዓ.ም በመንግሥት ታጣቂዎች ጉደር ከተማ ውስጥ በጥምቀት በዓል ላይ በጥይት ተመትቶ ጉደር ሆስፒታል ከገባ በኋላ ለከፍተኛ ሕክምና አዲስ አበባ ሕክምና ላይ ይገኛል፡፡



ጉልማ መንገሻ

38. **አቶ ለቺሳ በሬቻ፣** ኅዳር 30 ቀን 2008 ዓ.ም ከቀኑ በ9:30 ከኮምቦልቻ ወደ ጌዶ 30 መንገደኞችን አሳፍሮ መኪና በማሽከርከር ላይ ሳለ ቴሌ የምትባል አካባቢ ላይ ሲደርስ በታጠቁ የፌደራል ፖሊስ አባላት እርሱም ተሳፋሪዎቹም በአሠቃቂ ሁኔታ ተደብድበዋል፡፡ ገንዘብና ተንቀሳቃሽ ስልኮቻቸውን ተነጥቀዋል፡፡ ከደረሰባቸው ጉዳት የተነሣ ደማቸው በከፍተኛ ሁኔታ እየፈሰሰ ለተወሰነ ጊዜ ያህል በእሥር ላይ አቆይተዋቸዋል፡፡

39.ተማሪ ጥላሁን ግርማ፣ ዕድሜ 14፤ ኅዳር 30 ቀን 2008 ዓ.ም ከቀኑ በ8:30 ጨሊያ ወረዳ ባቢች 01 ቀበሌ ሸንኮራ አገዳ በመነገድ ላይ ሳለ ደረቱና ቀኝ እጁ ላይ በሁለት ጥይት ተመትቷል፡፡



ጥላሁን ግርማ

40. ሕፃን ኤሊያስ አራርሳ ጥላሁን እድሜው 8 ሲሆን በ11/06/2008 ዓ.ም. በግምት ከጠዋቱ 3 ሰዓት አካባቢ በታጠቁ የመንግስት ሀይሎች የቀኝ ታፋው ላይ በጥይት ተመትቶ አምቦ ሆስፒታል በህክምና ላይ ይገኛል፡፡

41. ኢቱ ነጋሴ አራርሳ እድሜ 15 በ11/06/2008 ዓ.ም. በግምት ከጠዋቱ 3 ሰዓት አካባቢ በታጠቁ የመንግስት ሀይሎች የግራ እግሯን በጥይት ተመትታ አምቦ ሆስፒታል በህክምና ላይ ትገኛለች፡፡

**በጥይት ተመትተው እና ከፍተኛ ድብደባ ደርሶባቸው በወሊሶ ቅዱስ ሉቃስ ሆስፒታል በተለያዩ ጊዜያት ተኝተው የታከሙ ተጎጂዎች ስም ዝርዝር**

| ተ.ቁ. | ሙሉ ስም | ወረዳ | ቀበሌ |
|---|---|---|---|
| 1 | አቢሳ ድሪባ ኤጀታ | ወሊሶ | ዲለላ |
| 2 | ማሞ ባህሩ አዱኛ | ወሊሶ | ዲለላ |
| 3 | ባይሳ መርጋ አብዲሳ | ወሊሶ | ዲለላ |
| 4 | ለማ ተረፈ | ወንጪ | ወንጪ |
| 5 | ቀንአ ዲራራ | ወንጪ | ወንጪ |
| 6 | ድሪባ ብርሃኑ | ወሊሶ | አቢ |
| 7 | አየለ ኩምሳ | ወሊሶ | |
| 8 | ጉዲሳ አዱኛ | ወሊሶ | |
| 9 | መጋሪ ተሾመ | ወሊሶ | |
| 10 | የዶ ሞረዳ | ወሊሶ | |
| 11 | ተሻለ ተክሉ | ወሊሶ | |
| 12 | ዲሪባ ረሠላ | ወሊሶ | |
| 13 | ነብሶ ሀይሉ | ወሊሶ | 01 |
| 14 | አብርሃም ሀይሌ ደጉ | ወሊሶ | |
| 15 | ደገፋ ከበደ | ወሊሶ | 02 |
| 16 | ቡሎ ፍቃዱ | ወሊሶ | |

## 5.3 ማሠቃየት/ድብደባ

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ዕድሜ | ድብደባው የተፈጸመበት ቀን | ድብደባው የተፈጸመበት ቦታ | የጉዳቱ ዓይነት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መ/ር አመታ ቱፋ | 32 | 29/03/08 | ጌዶ | የቀኝ እግራቸው ተሰብሯል |
| 2 | መ/ር ዳዊት ተካ | 28 | ›› | ›› | ›› |
| 3 | አቶ ጦና | 45 | ›› | ›› | ጀርባቸው ላይ ጉዳት ደርሷል |
| 4 | አቶ አጥናፉ | 50 | ›› | ›› | የቀኝ እጃቸው ተሰብሯል |
| 5 | አቶ ደረጀ ሉሉ | 35 | ›› | ›› | ከደረሰባቸው ጉዳት አገግመዋል |
| 6 | ዲያቆን ዳዊት ጋዲሳ | 28 | ›› | ›› | ማጅራቱና እግሩ ላይ የተደበደበ |
| 7 | ተማሪ ደምሴ ጋቢሳ ሒርጳ | 18 | 01/03/08 | ባቢች | መላ ሰውነቱን የተደበደበ |
| 8 | ተማሪ አዱኛ ተሰማ ሁንዴ | 20 | 22/03/08 | ቶኬ ኩታይ | ከደረሰበት ጉዳት አገግሟል |
| 9 | አቶ ጋሻው ፈይሳ | 28 | 22/03/08 | ›› | የግራ እግራቸው ተጎድቷል |
| 10 | አቶ ደሳለኝ ጉዲሳ ኦላና | 37 | 22/03/08 | ›› | የግራ እጃቸው ተጎድቷል |
| 11 | ተማሪ አቡሽ በዳዳ ሀዊሶ | 24 | 22/03/08 | ›› | ቀኝ ጉልበቱ ተጎድቷል |
| 12 | አቶ ፈየራ ጫሜሳ | 34 | 22/03/08 | ›› | ሆስፒታል ገብተው የወጡ |
| 13 | አቶ ጉልማ መንገሻ | 27 | 11/05/08 | ›› | ጭንቅላቱና ግራ እግሩ ተጎድቷል |
| 14 | አቶ ግርማ ታደሰ | 55 | 27/03/08 | ሜታሮቢ /ሸኖ/ | በሰደፍ የተደበደቡ |
| 15 | አቶ ሞሲሳ ዳዴ | 50 | 27/03/08 | ›› | ›› |
| 16 | አቶ በየነ ረጋሳ | 40 | 27/03/08 | ›› | ›› |
| 17 | አቶ በቀለ ጋዲሳ | 45 | ›› | ›› | ተደብድበው በእሥር ላይ የሚገኙ |
| 18 | አቶ ወንዳጥር ከበደ | 30 | 06/04/08 | ደንቢ ዶሎ ከተማ | የሕክምና ክትትል ላይ ናቸው |
| 19 | አቶ ገቢሳ ላሜሳ | 40 | 07/04/08 | ደንቢ ዶሎ ከተማ | ተደብድበው ታክመው ድነዋል |
| 20 | አቶ ግርማ አዳል | 26 | 25/04/08 | ግንደበረት አቡና ከተማ | በኦሮሚያ ፖሊሶች ተደብድቧል |
| 21 | አቶ ጆንሴ ዴሬሳ ሞሚቻ | 35 | 07/04/08 | ግንደበረት አቡና ከተማ | በኦሮሚያ ፖሊሶች ተደብድቧል |
| 22 | አቶ አስመራ | - | - | ግንደበረት አቡና ከተማ | በኦሮሚያ ፖሊሶች ተደብድቧል |

ባይሳ መርጋ



## 5.4. እሥራት

| ተ.ቁ | የታሣሪው ስም | ዕድሜ | የታሠረበት ቀን | የታሠረበት ቦታ | አሁን ያለበ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መምህር ከበደ ጨመዳ | 35 | 29/03/08 | ጌዶ ማረሚያ ቤት | በየትኛው እሥር ቤት እንዳሉ አይታወቅም |
| 2 | አቶ ደረጀ ሉሉ | 35 | 29/03/08 | ›› | ከእሥር ተለቅቀዋል |
| 3 | ወጣት ደምሴ ጋቢሳ | 22 | 01/03/08 | ባቢች ማረሚያ ቤት | ከእሥር ቢለቀቅም ክትትል ይደረግበታል |
| 4 | አቶ ተሰማ ሁንዴ | 40 | 22/04/08 | ቃሊቲ ማረሚያ ቤት | በእሥር ላይ የሚገኙ |
| 5 | ተማሪ ሁንዴ | 18 | 22/04/08 | ቶኪ ኩታይ ማረሚያ ቤት | ከእሥር ተለቅቀዋል |
| 6 | ዋቅጅራ አመና ማሞ | 17 | 04/05/08 | ሰንቀሌ ፖሊስ ማሠልጠኛ | በእሥር ላይ የሚገኝ |
| 7 | አቶ መንግሥቱ ጉዲሳ | 25 | 22/03/08 | ቃሊቲ ማረሚያ ቤት | ›› |
| 8 | ወጣት ደረጀ | 20 | 22/03/08 | ›› | ›› |
| 9 | አቶ ከበደ | 26 | 22/0308 | ቶኪ ኩታይ ማረሚያ ቤት | ከእሥር ተለቅቋል |
| 10 | ሰለሞን ነጋሳ ጀልቀባ | 17 | 22/03/08 | ሰንቀሌ ፖሊስ ማሠልጠኛ | በእሥር ላይ የሚገኙ |
| 11 | አቶ ተሰማ ወንዴ | 42 | 22/03/08 | ቶኪ ኩታይ ማረሚያ ቤት | ›› |
| 12 | አቶ ኃይሉ በድአኔ | 48 | 22/03/08 | ›› | ›› |
| 13 | አቶ ተሬሳ ደብአስ | 46 | 22/03/08 | ›› | ›› |
| 14 | አቶ ቱጁባ ሬፌራ | 47 | 22/03/08 | ›› | ›› |
| 15 | ወጣት ፊየራ መረራ | 17 | 11/05/08 | ›› | ›› |
| 16 | ወጣት ብርሃኑ ታመነ | 16 | 11/05/08 | ›› | ›› |
| 17 | ወጣት ሃዊ ጉቱ | 18 | 18/05/08 | ›› | ›› |
| 18 | ተማሪ አማኑኤል ኤፍሬም | 17 | 02/04/08 | ነቀምቴ ማረሚያ ቤት | በእሥር ላይ ይገኛሉ |
| 19 | ተማሪ ጫራ ጌታሁን | 20 | 02/04/08 | ነቀምቴ ማረሚያ ቤት | በእሥር ላይ ይገኛል |
| 20 | መሐዲ ኦዶሞ ኢብሮ | 21 | 12/05/08 | መኢሶ ወረዳ ፖሊስ | በእሥር ላይ ይገኛል |
| 21 | ጀማሎ አሊዬ አብዱራህማን | 33 | 12/05/08 | መኢሶ ቻይና ካምፕ | ›› |
| 22 | አብዲ ኢብሮ አጡሬ | 35 | ›› | ›› | ›› |
| 23 | በዳሶ አብደላ በይሶ | 27 | ›› | ›› | ›› |
| 24 | አረሽ መሐመድ ወዳይ | 19 | ›› | ›› | ›› |
| 25 | አብዲ ኡስማን በዳሶ | 22 | ›› | ›› | ›› |
| 26 | ኤልያስ ሁሴን | 22 | ›› | ›› | ›› |
| 27 | አብዲ ሁሴን አሕመድ | 18 | ›› | ›› | ›› |
| 28 | ሀሼሞ አላይ ሰዒድ | 23 | 15/05/08 | ›› | ›› |
| 29 | ኢሴ አብዱላሂ | 42 | ›› | ›› | ›› |
| 30 | መሐመድ (ፎሎል) | 21 | 13/05/08 | ›› | ›› |
| 31 | ላሎ አሊ አብዶ | 43 | 15/05/08 | መኢሶ ቻይና ካምፕ | በእሥር ላይ ይገኛል |
| 32 | ሞሚና አሚን | 38 | 14/05/08 | ›› | ›› |
| 33 | ሚስሩ (ኮራ) | 33 | 13/05/08 | መኢሶ ወረዳ ፖሊስ | ›› |
| 34 | አብዶ ሼካ | 21 | 13/05/08 | መኢሶ ወረዳ ፖሊስ | በእሥር ላይ ይገኛል |
| 35 | አብዲ | 19 | 13/05/08 | ›› | ›› |
| 36 | ናስር ኡሼ | 32 | 16/05/08 | ›› | ›› |
| 37 | የዶታ | 24 | ›› | ›› | ›› |
| 38 | ሙእዲን ኤርሚያስ | 21 | 17/04/08 | መሰላ ፖሊስ ጣቢያ | ›› |
| 39 | አልዬ ጀማል | 30 | ›› | ›› | ›› |
| 40 | አብዱ ማሊን | 28 | ›› | ›› | ›› |
| 41 | የሱፍ ጁሀር | 25 | ›› | ›› | ›› |
| 42 | ግዛቸው ደሳ | 70 | | ግንደበረት ወረዳ አቡና ወረዳ | በእሥር ላይ |
| 43 | ፊጣ ገሠሠ | | | ›› | ›› |
| 44 | ወርቁ አበበ | | | ›› | ›› |
| 45 | ለታ ወርዶፋ | | | ›› | ›› |

| ተ.ቁ | የታሣሪው ስም | ዕድሜ | የታሠረበት ቀን | የታሠረበት ቦታ | አሁን ያለበ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| 46 | መሱ ደቻሳ | | | ›› | ›› |
| 47 | ዳባ ደቻሳ | | | ›› | ›› |
| 48 | ማሞ ደቻሳ | | | ›› | ›› |
| 49 | ሃጫሉ | | | ›› | ›› |
| 50 | ተሾመ ረጋሳ | | | አ.አ ማዕከላዊ | በእሥር ላይ |
| 51 | በዩጫ ዋቃ | | | አ.አ ማዕከላዊ | ›› |
| 52 | ገላና በሻና | | 29/05/08 | ጀልዱ ፖሊስ ጣቢያ | ›› |
| 53 | ባጨ በዳዳ | | ›› | ›› | ›› |
| 54 | ጉዳ ዋቅቶላ | | 29/05/08 | ጀልዱ ፖሊስ ጣቢያ | በእሥር ላይ |
| 55 | ዘበናይ ከበደ | | ›› | ›› | ›› |
| 56 | ሀብታሙ ተክሉ | | ›› | ›› | ›› |
| 57 | ዘሩ አበራ | | ›› | ›› | ›› |
| 58 | ሮዛ ገቢሳ | | ›› | ›› | ›› |
| 59 | ራቢራ ቡልቱሜ | | ›› | ›› | ›› |

## በወሊሶ ከተማ ህገ ወጥ እስር የተፈጸመባቸው ሰዎች

| ተ.ቁ. | ሙሉ ስም | የታሰሩበት ቀን | ዕድሜ | ሥራ | አሁን ያሉበት ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| 60 | ናኦል ዲባባ | 27/03/08 | 23 | ተማሪ | ማእከላዊ |
| 61 | ሰአዳ ማቲ | 27/03/08 | 22 | ተማሪ | ማእከላዊ |
| 62 | ግርማ ጫላ | 27/03/08 | 24 | ተማሪ | ማእከላዊ |
| 63 | ጸጋዬ እንዳለ | 27/03/08 | 23 | ተማሪ | ማእከላዊ |
| 64 | አለሙ ኡሩማ | 27/03/08 | 25 | ተማሪ | ማእከላዊ |
| 65 | ግርማ ኡርጋ | 27/03/08 | 24 | ተማሪ | ማእከላዊ |
| 66 | እንዳልካቸው ገነነ | 27/03/08 | 22 | ተማሪ | ማእከላዊ |
| 67 | ወርቅነህ ከበደ | 23/03/08 | 40 | የህግ ባለሙያ | ማእከላዊ |
| 68 | አቡሽ ፈጠማ | 23/03/08 | 19 | ተማሪ | ማእከላዊ |
| 69 | መ/ር ፍቃዱ ደባ | 23/03/08 | 35 | መ/ር | ማእከላዊ |
| 70 | ቦጋለች በቀለ | 27/03/08 | 37 | የቤት እመቤት | ማእከላዊ |
| 71 | ዳንኤል ወርቅነህ | 27/03/08 | 20 | ተማሪ | ማእከላዊ |
| 72 | ዳንኤል ማንዴቦ | 27/03/08 | 21 | ተማሪ | ማእከላዊ |
| 73 | ፈየራ ሽጉጤ | 22/04/08 | 28 | የመንግስት ሰራተኛ | ወሊሶ ማረሚያ ቤት |
| 74 | ታምሩ ቦጋለ | 22/04/08 | 30 | መ/ር | ወሊሶ ማረሚያ ቤት |
| 75 | ሲሳይ አለሙ | 22/04/08 | 30 | መ/ር | ወሊሶ ማረሚያ ቤት |
| 76 | ወጋራ ሽለመ | 22/04/08 | 32 | መ/ር | ወሊሶ ማረሚያ ቤት |
| 77 | ድሪባ ጀቤሳ | 22/04/08 | 22 | መምህር | ወሊሶ ማረሚያ ቤት |
| 78 | ታምሩ በቀለ | 22/04/08 | 28 | የቴክኒክ ሙያ መ/ር | ወሊሶ ማረሚያ ቤት |
| 79 | ፀጋዪ እንዳለ | 22/04/08 | 29 | የግል ስራ | ወሊሶ ማረሚያ ቤት |

## ከአመያ ወረዳ ድሬ እንጭኒ እና ጉርትራ የታሰሩ

| ተቁ | ሙሉ ስም | እድሜ | ስራ | አሁን ያሉበት ሁኔታ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 80 | ፋፋ ፈዬራ ያዴሳ | 30 | የመድረክ ጸኃፊ | ወሊሶ ማ/ቤት | ማእከላዊ ተወስደዋል |
| 81 | ደመና ይማኑ ቶባ | 31 | አርሶ አደር | ወሊሶ ማ/ቤት | |
| 82 | ሌንጭ ይመኑ ቶባ | 23 | በግል | ወሊሶ ማ/ቤት | |
| 83 | ዘሪሁን ታዮ | 30 | በግል | ወሊሶ ማረሚያ ቤት | 11/04/08 የታሰረ |
| 84 | አዳሙ ዳኘ | 24 | በግል | ወሊሶ ማረሚያ ቤት | 04/04/08 የታሰረ |

## 5.5. የደረሱበት የማይታወቅ

| ተ.ቁ | ስም | ዕድሜ | የጠፋበት ቀን | አሁን ያለበት ሁኔታ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወጣት ደምሴ ጋቢሳ ሄርጳ | 22 | 01/03/08 | በጸጥታ ኃይሎች የተሰወረ | |
| 2 | መ/ር ከበደ ጨመዳ | 45 | 29/03/08 | ›› | |
| 3 | አቶ አዲሱ አክሊል | 40 | 01/03/08 | የት እንዳሉ አይታወቅም | |
| 4 | አቶ ፈየራ ጉደታ | 42 | 22/03/08 | ›› | |
| 5 | አቶ ዮሐንስ ጉታ | 40 | 07/04/08 | ›› | |
| 6 | አቶ መንጌ ጉደታ | | 01/04/08 | ›› | |

### ከቀዬአቸው ከአመያ ወረዳ ተፈናቅለው ያሉበት ያልታወቀ

| ተ.ቁ. | ሙሉ ስም | እድሜ | ስራ |
|---|---|---|---|
| 7 | ሞቱማ ገየራ | 30 | አርሶ አደር |
| 8 | ገላና ይመኑ ቶባ | 26 | አርሶ አደር |
| 9 | ፈዬራ ይመኑ ቶባ | 24 | ተማሪ |
| 10 | ኡመታ ይመኑ ቶባ | 23 | የግል ተዳዳሪ |
| 11 | ታሜ ልኪሳ ቶባ | 27 | ተማሪ |
| 12 | ሌንጨ ይመኑ ቶባ | 25 | የግል |

## 5.6. የንብረት ውድመትና መፈናቀል

የአዲስ አበባና የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን የተቀናጀ ማስተር ፕላንን ባለመቀበል በተለያዩ የኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች ከተቀሰቀሰው ሕዝባዊ ተቃውሞ ጋር በተያያዘ በመንግሥት ኃይሎች የተወሰደው እርምጃ ዜጎችን ለሞት፣ ለአካል ጉዳት፣ ለእሥርና ለመሠወር ዳርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተቃውሞ እንቅስቃሴውን ተከትሎ በኦሮሚያ ክልል በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን አመያ ወረዳ በተለያዩ ቀበሌዎች ኩኖ ቁሊት (ቀርሳ ቁሊት)፣ ወረ ወገሪ (በሬዳ) እንዲሁም አብሌ መድኃኔዓለም ከ30ዓመታት በላይ ሲኖሩ የነበሩ ነዋሪዎችን ታኅሣሥ 02 ቀን 2008ዓ.ም ሌሊት ጀምሮ የአዲስ አበባን ማስተር ፕላን በመቃወም ከወጡ ሰላማዊ ሰልፈኞች መካከል ጥቂቶቹ በአካባቢው በሚኖሩ የአማራ ብሔር ተወላጆች መኖሪያ ቤታቸውን ከነሙሉ ንብረታቸው አቃጥለውባቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት በርካታ ሰዎች ተፈናቅለው ወደ ኹዳድ2፣ ዳርጌ፣ ዋልጋ ከተማና ወልቂጤ ከተሞች ተሰድደዋል፡፡ ከ300 በላይ አርሶ አደሮች ከኩኖ ቁሊት ቀበሌ ቤታቸው ሙሉ በሙሉ ተቃጥሎባቸው ወሊሶ ከተማ ‹‹ሁሉ ይማር›› ት/ቤት ውስጥ ለአንድ ሳምንት ያህል ተጠልለው ቆይተዋል፡፡ ቀይ መስቀልም ዕርዳታ ሲያደርግላቸው እንደነበር ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዳርጌና በኩዳድ1 ቀበሌም ቁጥራቸው ከ500 የማያንስ ተፈናቃዮች ከተለያዩ ቀበሌዎች በድንኳን ውስጥ መጠለላቸውን የሰመጉ ባለሙያዎች በቦታው በመገኘት አረጋግጠዋል፡፡ በአጠቃላይ የተቃጠለው ቤት ከ800 በላይ ሲሆን በዝርዝር ያገኘናቸው እንደሚከተለው ይቀርባል፡-

| ተ.ቁ | ቤት የተቃጠለበት ሰው ስም | የተቃጠለበት ቀበሌ | የተቃጠለበት ቀን | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አያልቅበት ዐይተህ ግዛ | በሮዳ ጩሉሎ | 02/04/08 ሌሊት | ሣር ቤት |
| 2 | ያብሩ ዘለቀ | ›› | ›› | ›› |
| 3 | ጌታው ሽታ | ›› | ›› | ›› |
| 4 | ለወጠኝ እሸቴ | ›› | ›› | ›› |
| 5 | ታደሰ ወ/ሃና | ›› | ›› | ›› |
| 6 | አቦዎይ ጭንቅል | ›› | ›› | ›› |
| 7 | አዳው ሰባዩ | ›› | ›› | ›› |
| 8 | አበረ ለማ | ›› | ›› | ›› |
| 9 | አውላቸው ሲሳይ | ›› | ›› | ›› |
| 10 | ሱረት ታደሰ | ›› | ›› | ›› |
| 11 | ጌታው እምዩ | ›› | ›› | ›› |
| 12 | ገዙ ባጥቂ | ›› | ›› | ›› |
| 13 | ደነቀው በቀለ | ›› | ›› | ›› |

| ተ.ቁ | ቤት የተቃጠለበት ሰው ስም | የተቃጠለበት ቀበሌ | የተቃጠለበት ቀን | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 14 | ሁሉም ታዬ ደነቀው | ›› | ›› | ›› |
| 15 | ሻምበል አየለ | ›› | ›› | ›› |
| 16 | ላውጋለት አልታዬ | ›› | ›› | ›› |
| 17 | ደምሴ መብሬ | ›› | ›› | ›› |
| 18 | ጌታቸው ነጋሽ | ›› | ›› | ›› |
| 19 | አሰማ ጌታሁን | ›› | ›› | ›› |
| 20 | አያሌው ግርማ | ›› | ›› | ›› |
| 21 | አሰበ ቸርነት | ›› | ›› | ›› |
| 22 | ፍቃዱ ጠቅል | ›› | ›› | ›› |
| 23 | ካብታሙ ጫኑ | ›› | ›› | ›› |
| 24 | አበረ ክፍለ ማርያም | ›› | ›› | ›› |
| 25 | መንገሻ ተክለማርያም | ›› | ›› | ›› |
| 26 | ገላምጤ ታደሰ | ›› | ›› | ›› |
| 27 | ወንድም ስሻ ገብረየስ | ›› | ›› | ›› |
| 28 | ግዛቸው እንግዳወርቅ | ›› | ›› | ›› |
| 29 | መሪጌታ ኪዳነወርቅ | ›› | ›› | ›› |
| 30 | ጥሩነህ ፍለማርያም | በሮዳ ጨሉሎ | 02/04/08ዓ.ም | ሌሊት |
| 31 | ጌታው ምንዳ | ›› | ›› | ›› |
| 32 | አየለ አበረ | ›› | ›› | ›› |
| 33 | እዋወይ አብዬ | ›› | ›› | ›› |
| 34 | በለጠ ክፍለማርያም | ›› | ›› | ›› |
| 35 | እንደሻው ክፍለማርያም | ›› | ›› | ›› |
| 36 | ንጉሤ ወርቃለማሁ | ›› | ›› | ›› |
| 37 | ጎረምስ አማረ | ›› | ›› | ›› |
| 38 | ብሩ ወንድማገኝ | ›› | ›› | ›› |
| 39 | ሽፈራ አባበይ | ›› | ›› | ›› |
| 40 | ምሳዎይ ወንድማገኝ | ›› | ›› | ›› |
| 41 | አበበ ያብሩ | ›› | ›› | ›› |
| 42 | አባቦይ ታዬ | በሮ ሙሪያ ቀበሌ | 02/04/08 | ሌሊት |
| 43 | ጌታው ጠንክር | ›› | ›› | ›› |
| 44 | አስጨናቂ ታዬ | ›› | ›› | ›› |
| 45 | ጌታው መንግሥት | ›› | ›› | ›› |
| 46 | አግዘው ጉልቴ | ›› | ›› | ›› |
| 47 | ደጀን አሰግድ | ›› | ›› | ›› |
| 48 | ዐወቀ ቅጣው | ›› | ›› | ›› |
| 49 | ውድሰው በቀለ | ›› | ›› | ›› |
| 50 | ጌትዎይ በቀለ | ›› | ›› | ›› |
| 51 | ጌታው ማሞ | ›› | ›› | ›› |
| 52 | ዘለቃው ደረበ | ›› | ›› | ›› |
| 53 | ተሾመ አሰግድ | ›› | ›› | ›› |
| 54 | በሱፍቃድ መንገሻ | በሮ ሙሪያ ቀበሌ | 02/04/08 | ሌሊት |
| 55 | አሰፋ አግማስ | ›› | ›› | ›› |
| 56 | ስንታየሁ ተሰማ | ›› | ›› | ›› |

ነ

| ተ.ቁ | ቤት የተቃጠለበት ሰው ስም | የተቃጠለበት ቀበሌ | የተቃጠለበት ቀን | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 57 | አበበ ዘነበ | ›› | ›› | ›› |
| 58 | አውራሪስ በዜ | ›› | ›› | ›› |
| 59 | ዓለሙ ማሙዬ | ›› | ›› | ›› |
| 60 | ወልዴ አበራ | ›› | ›› | ›› |
| 61 | ቻለው ዓለሙ | ›› | ›› | ›› |
| 62 | አስቻለው ወንድራድ | ›› | ›› | ›› |
| 63 | ደስታው ሙላት | ›› | ›› | ›› |
| 64 | አዲሴ ሙላት | ›› | ›› | ›› |
| 65 | ተረፈ ላቀው | ›› | ›› | ›› |

በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን በአመያ ወረዳ በተለያዩ ቀበሌዎች የአዲስ አበባን ማስተር ፕላን ማስፋፋትን ባለመቀበል በተነሣው ተቃውሞ በሰላማዊ ሰልፉ የተሳተፉ ጥቂት የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች ለበርካታ ዓመታት በአካባቢው ከሕዝቡ ጋር አብረው የኖሩትን የአማራ ተወላጆች ቤት አቃጥለዋል፤ በቤት ውስጥ የነበረ ለሽያጭ የተዘጋጀ በርበሬና የተለያዩ የእህል ዓይነቶች ምርት ወድሟል፡፡ ማሳ ላይ የነበረ እህልም ተቃጥሏል፡፡ በኩኖ ቁሊት ቀበሌ ላይ፣ የአማራ ተወላጆች በወሰዱት የአጸፋ እርምጃ ደግሞ ቁጥሩ 96 የሚሆን የኦሮሞ ተወላጆች ቤትም ተቃጥሏል፡፡ ይህ ሕዝብን በሕዝብ ላይ የማነሳሳት ድርጊት የሚፈጸመው በዋነኛነት በጥቂት የራሳቸው ያልሆነውን መሬትና ኃብት ለመንጠቅና ያለአግባብ ለመክበር በሚፈልጉ የአካባቢ ሀብታሞች አነሳሽነትና መሪነት እንዲሁም በመሰል ጥቅም ፈላጊ ባለሥልጣኖች አይዞህ ባይነት መሆኑን ተጎጂዎች ገልጸዋል፡፡

በአመያ ወረዳ በኦሮሞና በአማራ ሕዝብ መካከል ምንም ዓይነት ጸብ ሳይኖር ተግባብተው በጋብቻና በወዳጅነት አብረው ሲኖሩ ቆይተዋል፡፡ አሁንም እየኖሩ ነው፡፡ ዳሩ ግን ጊዜና ሁኔታውን የሚጠቀሙ ጥቂት የአካባቢ ባለሥልጣኖችና ሀብታሞች ለራሳቸው ልዩ ጥቅም በመፈለግ ሲፈጥሩት የቆዩትና እየፈጠሩት ያለው ችግር በአማራና በኦሮሞ ተወላጆች የጋራ ስብሰባ የተወገዘ ሲሆን ወደፊት እንዲህ ዓይነት ችግር እንዳይፈጠር በሁለቱም በኩል ሽማግሌዎች በመምረጥ በአሁኑ ወቅት በሰላም እየኖሩና የተቃጠለውንም ቤት በጋራ እየሠሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ችለናል፡፡

## 5.7. የወደመ የመንግሥት ንብረት

የአዲስ አበባና የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን የተቀናጀ ማስተር ፕላንን ባለመቀበል በተለያዩ የኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች ከተቀሰቀሰው ሕዝባዊ ተቃውሞ ጋር በተያያዘ የተለያየ የመንግሥትና የሕዝብ ንብረት ወድሟል፡፡ ይህንንም ችግር የምዕራብ ሸዋ ዞን፣ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን ቡራዩ ከተማ አስተዳደር፣ የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን የሱሉልታ ከተማ አስተዳደርና የፖሊስ ኃላፊዎችን በአጠቃላይ ስለደረሰው ችግር ማብራሪያ እንዲሰጡን በየቢሯቸው ተገኝተን አነጋግረን የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውናል፡፡

- ስለደረሰው የሰው ሕይወት መጥፋት እየተጣራ መሆኑንና ምርመራው ሲጣራ እንደሚገለጽ፤
- ሦስት የፖሊስ ባልደረቦች ግንደበረት ወረዳ አቡና ከተማ መገደላቸውንና ሁለት የፖሊስ አባላትም በጥይት ተመትተው ፖሊስ ሆስፒታል በሕክምና ላይ መሆናቸውን፣
- 142 ከምዕራብ ሸዋ ዞን የተለያዩ ወረዳዎች የመጡ የሕግ እሥረኞች በአምቦና በአዲስ ዓለም ማረሚያ ቤት እንደሚገኙ፣
- የገበሬ ማኅበር ጽ/ቤቶች፣ ንዑሥ ፖሊስ ጣቢያዎች፣ የገበሬዎች ማሠልጠኛ አዳራሾች በተለያዩ አካባቢዎች ጉዳት እንደደረሰባቸው፣
- ንብረትነታቸው የዳንጎቴ ሲሚንቶ ፈብሪካ የሆኑ ከ10 በላይ መኪናዎች መቃጠላቸውን፣

- አንድ የሕዝብ ማመላለሻ የከተማ አውቶብስ 1,700,000 ብር የሚገመት መኪና መቃጠሉን ገልጸውልናል፡፡
- የአዲስ አበባና የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን የተቀናጀ ማስተር ፕላንን ባለመቀበል በተለያዩ የኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች ከተቀሰቀሰው ሕዝባዊ ተቃውሞ ጋር በተያያዘ የጠፋውን የሰው ሕይወት፣ የወደመውን ንብረትና ችግሩ አሁን ስለሚገኝበት ደረጃ እንዲገልጹልን የኢፌዴሪ የመንግሥት ኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት፣ የኢፌዴሪ ፌዴራል ፖሊስ፣ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስተዳደርና የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ፖሊስ ኮሚሽንን በአካል ተገኝተን ጠይቀናል፡፡ ነገር ግን ገና መረጃውን እያጠናቀሩ በመሆናቸው አሁን መልስ ሊሰጡን እንደማይችሉ ገልጸውልናል፡፡

## 6. ማጠቃለያ

በዚህ የሰመጉ 140ኛ ልዩ መግለጫ የቀረቡት የሞት፣ የአካል ጉዳት፣ ንብረት ማውደም፣ የእሥራትና የመሰወር እንዲሁም ሌሎች የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች አስተማማኝ ማስረጃ የተገኘባቸው ብቻ ናቸው፡፡ ነገር ግን በሕዝቡ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ እንቅስቃሴ ወቅት የተገደሉ፣ የተጎዱ፣ የታሠሩና የወደሙ ንብረቶች እጅግ በጣም ከፍተኛ እንደሆኑ ይገመታል፡፡ ጉዳት በደረሰባቸው አካባቢዎች ባለሙያዎቻችን ተዘዋውረው እንዳረጋገጡት ከፍተኛ የሆነ የፖሊስና የሠራዊት ኃይል በየአካባቢው በብዛት በመኖሩ ሕዝቡ መረጃ በተለይም ማስረጃ ለመስጠት በከፍተኛ ፍርሃት ውስጥ ይገኛል፣ ማንንም ሰው ለማመን ተቸግሯል፡፡

ይህ ሪፖርት በሚጠናቀርበት ወቅት በምዕራብ አርሲ በአጄ፣ ሻሸመኔ፤ ኮፈሌና አካባቢው፣ በምዕራብ ወለጋ በአርጆና አካባቢው፣ በምዕራብ ሸዋ አምቦ እና ጉደር ህዝባዊ ተቃውሞው እንደቀጠለ ነው፡፡ በታጠቁ የመንግስት ሀይሎች የሰው ህይወት እየጠፋ፣ የአካል ጉዳት እየደረሰ፣ እስራትና ድብደባ እየተፈጸመ እንደሚገኝ ከየቦታው ለሰመጉ መረጃዎች እየደረሱ ነው፡፡ የመንግሥት ታጣቂ ኃይሎች በአምቦና በጀልዱ አስገድዶ መድፈር መፈጸማቸውን ከነዋሪዎች ለመስማት ችለናል፡፡ መርማሪዎቻችን ያነጋገሯቸው በርካታ ነዋሪዎች እንደገለጹት በአንዳንድ ቦታዎች የመንግሥት ታጣቂዎች ሕገ ወጥ የቤት ለቤት አሰሳ ሌሊት ላይ የሚያደርጉ ሲሆን፣ በፍተሻ ወቅት የሚያገኙትን ንብረት ይወስዳሉ፣ በዜጎች ላይ ከፍተኛ የሆነ ድብደባ ይፈጽማሉ፣ ዛቻና ማስፈራሪያ እንዲሁም ስድብ ይሰነዝራሉ፡፡

መንግሥት ከላይ ለተገለጹት ሮሮዎችና አቤቱታዎች ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፤ ጉዳዩ በገለልተኛ አካል እንዲጣራ፣ ችግሩን የፈጠሩት በሕግ እንዲጠየቁ እንዲያደርግ፣ ተጎጂዎች በአግባቡ እንዲካሱና ለወደፊቱም እንዲህ ዓይነት ችግሮች እንዳይከሰቱ የመከላከልና ጥበቃ የማድረግ ኃላፊነቱን እንዲወጣ ሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

በምዕራብ አርሲ ዞን በተለያዩ ወረዳዎች የሚገኙ የሃይማኖት ተቋማት ማለትም የኦርቶዶክስ፣ የፕሮቴስታንትና የካቶሊክ አብያተ ክርስትያናት ተቃጥለዋል፡፡ ድርጊቱ የተፈጸመው በማንም ይሁን በማን በአጭሩ ካልተገታ፣ በሀገርና በሕዝብ ሰላምና መረጋጋት እንዲሁም በአንድነት ላይ የከፋ አደጋ ስለሚያስከትል እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት በአስቸኳይ እንዲቆም ሰመጉ ያሳስባል፡፡ መንግሥትም አጥፊዎችን በሕግ እንዲጠየቁ እንዲያደርግ ሰመጉ ይጠይቃል፡፡

ሰመጉም ወደፊት የሰብዓዊ መብቶች ቀውስ በተፈጠረባቸው በሁሉም የኦሮሚያ አካባቢዎች ከፍተኛና ሰፊ የማጣራት ሥራ መሥራት እንደሚኖርበት ያምናል፡፡ ስለሆነም የተጎጂዎች ቤተሰቦች፣ ተጎጂዎች እንዲሁም ለሰብዓዊ መብት መከበር አስተዋጽዖ ለማድረግ የምትፈልጉ ዜጎች ሁሉ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን ለሰመጉ ያለፍርሐት እንድታደርሱና አቤቱታዎችን እንድታቀርቡ ሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡ እንዲሁም ይህንን የሰመጉን ጥረት የምትደግፉ ዜጎችም ሰመጉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ለማጣራትና ውጤቱንም ይፋ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ድጋፍ በማድረግ የዜግነትና የሰብዓዊነት ግዴታችሁን እንድትወጡ ሰመጉ በአክብሮት ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

## 7. ማሳሰቢያ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 15 ‹‹ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት አለው፡፡ ማንኛውም ሰው በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን አያጣም›› ተብሎ የተደነገገውን በመተላለፍ፡

- በተማሪዎችና በሕዝቡ ለቀረበው ጥያቄ በመንግሥት የተሰጠው መልስ በምንም መልኩና በማንኛውም መለኪያ በሰመጉ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣
- በተማሪዎችና በሕዝቡ በተቀሰቀሰው ሰላማዊ የተቃውሞ ሰልፍ ሰበብ የሕይወት፣ የአካል፣ የንብረት ጉዳት ያደረሱትና ጉዳቱ እንዲደርስ ያዘዙት ኃላፊዎች በአስቸኳይ ለሕግ እንዲቀርቡ፣
- በተማሪዎችና በሕዝብ ሰላማዊ ሰልፍ ምክንያት የታሠሩት በርካታ እሥረኞች በአስቸኳይ እንዲፈቱ
- ግድያ፣ የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ግለሰቦችና ቤተሰቦች ተገቢው ካሣ እንዲከፈል፣
- ለወደፊቱም በተማሪዎችና በሕዝቡ ለሚነሡ ሰላማዊ ሰልፎች የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 30/1/ እንደሚደነግገው ‹‹ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፡፡›› የሚለውን ድንጋጌ መንግሥት እንዲያከብርና ዜጎች በሰላማዊ መንገድ የሚጠይቁትን ጥያቄ መንግሥት ሰላማዊ መልስ እንዲሰጥ ሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

በሌላም በኩል ዜጎች በሰላማዊ መንገድ ጥያቄና ቅሬታ ለመንግሥት አካላት ማቅረብ መብታቸው ነው፡፡ መንግሥትም ዜጎች የሚያነሷቸውን የተለያዩ ቅሬታዎችና ጥያቄዎች በሰላማዊ፣ ሕጋዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ የማስተናገድ ግዴታ አለበት፡፡ ሆኖም ዜጎች ጥያቄና ቅሬታቸውን የማቅረብ መብታቸውን ሲጠቀሙም ሆነ መንግስት ጥያቄ የማስተናገድ ግዴታውን ሲወጣ የባለጉዳዮቹንና የሌሎች ዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ማክበርና ማስከበር አስፈላጊ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ በማናቸውም ምክንያትና ሰበብ ዜጎችን በዜጎች ላይ ማነሳሳት፣ ጥቃት መፈጸምና እርስ በርስ ማጋጨት ሊወገዝ ይገባል፡፡ ይልቁንም በብሔረሰቦችና በሃይማኖቶች መካከል ከመቼውም ጊዜ የበለጠ መቻቻል፣ መተሳሰብና መፈቃቀር እንዲኖር መንግሥት፣ ተቃዋሚ ኃይሎች፣ ዜጎች፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የብዙኃን መገናኛዎችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የበኩላቸውን አስተዋጽዖ  እንዲያደርጉ ሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

ለሰብዓዊ መብቶች  መከበር የቆማችሁ ዜጎች፣ ሐገር አቀፍናዓለም አቀፍ ተቋማትም መንግሥት የዜጎችን ሰብዓዊ መብቶች እንዲያከብር፣ እንዲያስከብረና እንዲያሟላ ከዚህ በታች በተገለጹት አድራሻዎች በመጻፍ ጥያቄና ግፊት እንድታደርጉ ሰመጉ ይጠይቃል፡፡

- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት**
  ፖ.ሳ.ቁጥር ፡- 80001፣ ኢ-ሜል፡- national.parliament@telecom.net.et፣
  ፋክስ ፡- (+251) 011 155-0400፣የስልክ ቁጥር ፡- (+251) 011 124-1000፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር ፡- 20122/1000፣ ኢ-ሜል ፡- kumashih@gmail.com
  ፋክስ ፡- (+251) 011 124-1208/011 124-2308፣
  የስልክ ቁጥር ፡- (+251) 011 122-3322፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 23698፣ ፋክስ ፡- (+251) 011 551- 8656፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 551-8186፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት :-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡-1031፣ ፋክስ፡- (+251) 011 122-6292፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 124-1155፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 5608፣ ኢ-ሜል፡- mofatr1@yahoo.com፣
  ፋክስ፡-(+251)011 551-1200፣
  የስልክ ቁጥር፡-(+251) 011 515-3204፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1370፣ ኢ-ሜል፡ justabr@ethionet.et፣
  ፋክስ፡- (+251) 011 551-7775፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 551-3620፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 2459፣ ኢ-ሜል፡ ombudsmaneth@ethionet.et፣
  ፋክስ፡- (+251) 011 553-2073፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 543-336፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1165፣ ኢ-ሜ፡ hrcom@ethionet.et፣
  ፋክስ፡ (+251) 011 550-4125፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 550-4031፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደራል ፖሊስ ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 199፣ የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 551-2744፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለሶማሌ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር 392፣ ፋክስ፡- (+251) 25 775-3429፣
  የስልክ ቁጥር፡ (+251) 257 75 34 29
  ጅግጅጋ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኦሮሚያ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 101769፣ ኢ-ሜል፡- oromiawiev@ethionet.et፣
  ፋክስ፡- (+251) 011 551-3642 / (+251) 011 551-9633፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 552-4247፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1546፣ ፋክስ፡- (+251) 046 220-2408፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 046 221-4778/ 046 220-5848፣
  ሐዋሳ፣ ኢትዮጵያ
- **ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 44፣ ፋክስ፡- (+251) 057 775-0814፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 055 7775-0109፣
  አሶሳ፣ ኢትዮጵያ
- **ለአማራ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1324፣ ፋክስ፡- (+251) 058 220-2511፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 058 220-2659፣
  ባሕርዳር፣ ኢትዮጵያ
- **ለትግራይ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 291፣ ፋክስ፡- (+251) 034 441-6564፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 034 441-6563፣
  መቀሌ፣ ኢትዮጵያ
- **ለጋምቤላ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 25፣ ፋክስ፡- (+251) 046 220-2408፣
  ጋምቤላ፣ ጋምቤላ

- **ለሐረሪ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 952 ፋክስ፡- (+251) 025 666-2530፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 025 666-1723 / 025 666-1746
  ሐረር፣ ኢትዮጵያ

**ሰመጉ የቆመው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መዳበር፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነው!!**

**ሰመጉ በአፍሪካ የሕዝቦችና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የታዛቢነት ቦታ አለው፤**
**የዓለም ዓቀፍ ፀረ-ስቃይ ድርጅት አባል እና**
**የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ፌዴሬሽን ኮርስፖንዲን አባልም ነው፡፡**